

**አፍሪካ የተጋረጠባት አደጋ**

በመለስ ዜናዊ (ጠ/ሚኒስትር)

9

**«መልካም ገፅታችን ቤቱ የት ነው...?»**

አቤ ቶኪቻው

10

**አፍሪካና የሙስና ደረጃ ሪፖርት**

በአለማየሁ ገ/ማርያም (ፕሮፌሰር)


4



# አውራምባ ታይምስ

... ቅርብ ይሁኑ

2ኛ ዓመት ቁጥር 92 ህዳር 22 ቀን 2002 ዋጋ 3.50 ብር

# ኮ/ል መንግስቱ ታሪካዊ መፅሐፍ ፃፉ

- እስካሁን ምላሽ ያላገኙ አወዛጋቢ ጉዳዮች
- ከቅድመ አብዮት እስከ ስደት ያሉ ሁነቶች
- በሌሉበት ሥለተፈረደባቸው የሞት ፍርድ
- ብዙ ስለተባለለት የዘር ሐረጋቸው 13


በውስጥ ገፆች

የአንድነት ጠቅላላ ጉባኤ በውዝግብ ሳይካሄድ ቀረ

ስዬ ወደ አንድነት- የገነቡትን ለማፍረስ ወይስ ያልዘሩትን ለማጨድ ?

«ጭስ የአለማችን ዋነኛ ገዳይ ሆኗል»

ለ90 የህዝብ ግንኙነት ኃላፊዎች ስልጠና ተሰጠ




# አንድነት ለጨረታ

አንድነት ከትናንት በስቲያ ባደረገው አጠቃላይ ጉባኤ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳንና አቶ ስዬ አብርሃን በተንደሉ የብሔራዊ ም/ቤት አባላት ምትክ አመራር አድርጎ የመረጠበትን አካሄድ __ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም__ ከጨረታ ጋር በማያያዝ የጉባኤውን ከደንብ ውጪ መጠራት፣ ለግለሰቦቹ የተሰጠውን ልዩ መብት ፀያፍ የሚያደርገውን ጉዳይና ጥርጣሬ የፈጠረባቸውን አንድ ሁነት በዚህ መጣጥፋቸው ይተነትኑታል።

3

## ኤዲቶሪያል

# ለዴሞክራሲና ለነጻነት መታገል ወይስ ዴሞክራሲና ነጻነትን መታገል?

በየትኛውም ዘመን፣ በማንኛውም የዓለም ክፍል የነበሩ፣ ያሉና የሚኖሩ ሰብአዊ ፍጡራን በሙሉ በሰብአዊነታቸው ብቻ የተጎናፀፏቸው መሰረታዊ መብቶች አሏቸው:: እነዚህም የመናገርና ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ፣ የመሰብሰብና በህግ ፊት እኩል የመዳኘ ት መብት፣ የእምነት ነፃነትና ይበጀኛል የሚሉትን የመምረጥ መብቶች ናቸው:: ሦስተኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት የነበሩት ቶማስ ጀፈርሰን በአጭር አገላለጽ አንድ አገር መንግስት የሚያስፈልጋት እነዚህን የማይገፈፉ መብቶች ዜጎች እየተጎናፀፏቸው እንዲኖሩ ለማስቻል ነው ብለዋል:: እነዚህ ተፈጥሯዊ መብቶቻችን እየተከበሩልን ነውን?ብለን አበክረን መጠየቅ ግድ የሚለን ሁኔታ ላይ እንገኛለን::

የመናገርና ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ፣ የመሰብሰብና በህግ ፊት እኩል የመዳኘት፣ በዴሞክራሲያዊ መንገድ የፈለጉትን የመምረጥና የመሳሰሉት ሰብአዊ መብቶች በኢትዮጵያ ሰማይ ስር ያሉበት ጠለላ በእርግጥ እነዚህ መብቶች እንዳይገሰሱ የሚታገሉልን ኃይሎች አሉን? የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶችና ግለሰቦች ባህርያዊ ሁኔታ ህዝቡ ያሉበትን ውስብስብና ማለቂያ የለሽ ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችል፣ ፍፁም ነፃና ዴሞክራሲያዊ አሰራሮችን የሚያጎለብት፣ ተልእኮና አላማዎቻችን የሚሏቸው መርሆዎቻቸው ፍትህን፣ ዴሞክራሲን፣ የህግ የበላይነትን ተጠያቂነትንና የመቻቻል ስርአትን ለማምጣት የሚያስችሉ ናቸው?በአገራችን ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችና ፖለቲከኞች/ገዢው ፓርቲም ተቃዋሚዎችም/ ለነፃነትና ለዴሞክራሲ የሚታገሉ ወይስ ነፃነትንና ዴሞክራሲን የሚታገሉ? ከግብራቸው በመነሳት የተወሰኑ ነጥቦችን እንመልከት::

ከኢህአዴግ እንነሳ:: ኢህአዴግ ሰኔ 24 ቀን 1983 ዓ.ም ሃያ ከሚያህሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ባካሄደው ኮንፍረንስ የሽግግር መንግስቱን ከመሰረተ በኋላ ላለፉት 20 ያህል አመታት በስልጣን ላይ ቆይቷል:: ስለቀጣዩ ጠ/ሚ/ር ማንነት ሳይቀር በገደምዳሜ በመግለጽ «ስልጣኑ ይቀጥላል» እያለን ነው:: እኛን የሚያሳስበን የኢህአዴግ በስልጣን የመቀጠል ያለመቀጠል፣ የቀጣዩ ጠ/ሚ/ር ማን መሆን ያለመሆንም አይደለም:: ከ1983ቱ ቻርተር መጽደቅ በኋላ የነበሩት 20 ዓመታት ምን ይመስሉ ነበር? ከአመታቱ

ርዝማኔ አንጻር ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ተረጋግጠዋል? ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች የሚፈለገውን ያህል አድገዋል? ለህግ የበላይነት ያለው ግንዛቤና ተገዢነት ምን ይመስላል? የሚሉና በመግቢያችን ላይ የጠቀስናቸው ዕውቅ መሪ እንዳሉት የማይገፈፉ መብቶቻችንን እንደተጎናፀፍን እንድንቀጥል የሚያስችለን ዋስትና አለ? ማረጋገጫዎቹስ ይህን ያመለክታሉ? የሚል ነው።

ምንም ሰምና ወርቅ የለውም። የሚመለስና ሊመለስም የሚገባ ነው ብለን እናምናለን። እናም እንጠይቅ።

ከሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መጠበቅ በተጨማሪ ኢህአዴግ እንደገዢ ፓርቲነቱ በኃላፊነት ከሚጠየቅባቸው ጉዳዮች አንዱ ዜጎች ራሳቸውን በምግብ እንዲችሉ አድርጓል ወይ? የሚለውን እንመልከት ዛሬ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎቻችንን በረሃብ አለንጋ እየተገረፉ ይገኛሉ። ርሃብ ኩሩ ስብዕናቸውን ገፎ የሌሎች እጅ ጠባቂ አድርጓቸዋል። ቀያቸውን ጥለው እየተሰደዱ ነው። በረሃብ የሞተ የለም ልንል አንችልም። ረሃብ ገዳይ ነውና። ደግሞም ጊዜ አይሰጥምና።ሁልጊዜ ተጠያቂነቱን በተፈጥሮ አየር መዛባት ላይ ማሳረፍ ኃላፊነት ካለበት ወገን ፈጽሞ አይጠበቅም።

የኢንዱስትሪው ዘርፍ በእንጭጭ ደረጃ ላይ ነው። ግብርናችን በዘመናዊ ዘዴዎች አልተቀየረም። ዛሬም የሞፈር ቀንበር ድግር ወገል ጥገኝነታችን ቀጥሏል። የትራንስፖርቱ ዘርፍ ዜጎች እፎይ የሚሉበት ሳይሆን የሚማረሩበት ሆኗል። የንግድ ስርአቱስ? ጠንካራ መዋቅር ያለው፣ የምጣኔ ሃብቱ አጋዥ ወይስ በዳዴ ደረጃ ላይ ያለና ተዋናዮቹም «ስግብግቦች»? በነፃ ገበያ ይመራል የተባለው ኢኮኖሚ በተዛባ ግንዛቤ ልቅ ስለተተወ ከሚዛናዊነትና ተወዳዳሪነት ይልቅ ቀማኛነትንና ህገ ወጥነትን እያመጣብን ነው። ይህ ሁሉ ሲሆንም ብልጭ ድርግም ከሚል እርምጃ በዘለለ ዘላቂነት ያለው የመፍትሄ አቅጣጫ አልተቀመጠም። በየትኛውም ዓለም ያለ መንግስት የመንግስትነት ግዴታ የሆነውን የመሰረተ ልማት አውታሮች መገንባት ብቻውን ህዝቡ ሊደርስባቸው የሚገባቸውን ስኬቶች ለማጣቱ ማካካሻ አይሆኑም እንላለን።

ባለፉት 20 ዓመታት ስልጣንና ኃላፊነትን መከታ ያደረጉ ምዝበራዎች፣ አድሎአዊ አሰራሮች፣ የፍትህ መዛባቶች፣ የህግና ስርአት ጥሰቶች ሲፈጸሙ የኖሩት ቃልና ተግባር ለየቅል በመሆናቸው ነው ብለን እናምናለን። ዓለም አቀፍ ተቋማት እነዚህን ሁነቶች አስመልክቶ የሚያመጧቸው ሪፖርቶች ምንም «ማስተባበያ» ይሰጥባቸው የቱንም ያህል «ተጋነዋል» የሚል መከራከሪያ ይቅረብባቸው በገዢው ፓርቲ ላይ የሚያነጣጥሩ የኃላፊነት ተጠየቆች ናቸው። መሰረታዊ የሆኑ፣ የማይጣሱና የማይገሰሱ፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችም ይከበሩ ስንል ዛሬም ጥሪያችንን እናቀርባለን። ስለቀጣዩ ጠ/ሚ/ር ማንነት መብሰልሰልም የእነዚህን መብቶች ልዕልና በማረጋገጥ መሰረት ላይ ብቻ ይሁን።

ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችስ? ለአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ ልማት፣ ለሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር፣ ለመድብለ ፓርቲ ስርአት እውንነት፣ ለህግ የበላይነትና ፍትህ መስፈን፤ በአጠቃላይም ለአንድ አገር ሁለንተናዊ እድገት የተቃዋሚዎች ሚና እጅግ ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል። የተቃዋሚዎች ሚና የገዢውን ፓርቲ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በመንቀፍ፣ አላማዎቻቸውን ለማሳካት የሚያስችሉ ርዕዮተ ዓለሞችን ወይም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ማዕከል በማድረግ አማላይ አማራጮችን ከማቅረብ በተጨማሪ በአገራዊ ፋይዳዎች ላይ በቀጥታ በመሳተፍ የህዝቡን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለመቅረፍ መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። በሌሎች አገራት ያሉ ተቃዋሚዎች ዜጎች ለሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸው እንዲታገሉ አርአያ ሆነው ያደራጃሉ። ነፃ ሕብረተሰብ እንዲፈጠር ይታትራሉ። በውስጣቸውም በስልጣን ላይ ካለው ፓርቲ የላቀ የመቻቻል፣ ልዩነቶችን በሃይል ሳይሆን በውይይት የመፍታት፣ ለማይገሰሱ መብቶች በተጨባጭ የመታገል ስርአት መኖሩን እንታገልለታለን ለሚሉት ህዝብ ወይም የህብረተሰብ ክፍል ያሳያሉ። የኢትዮጵያ የተቃውሞ ፖለቲካ ድርጅቶችና ፖለቲከኞች ከዚህ ትምህርት ይወስዱ ዘንድ ጥቂት ነገሮችን ማንሳት እንፈልጋለን።

በተቃውሞው ጎራ በመሰለፍ ላለፉት ሃያ ያህል አመታት የታገሉ፣ መስዋእትነት የከፈሉ፣ የአቅማቸውን አስተዋጽኦ ያበረከቱና እያበረከቱ ያሉ ፓርቲዎችና ግለሰቦች በአገር ውስጥም በውጪም እንዳሉ እንገነዘባለን። ሊበረታታ የሚገባው ተግባር ነው። ይሁንና ይህ የጥቂት ፓርቲዎች ወይም ግለሰቦች ሚና ከተቃዋሚዎች የሚጠበቀውን የላቀ ሚና እንደመወጣት ሊቆጠር አይችልም። ከዛ አልፎም አንዳንድ ተግባሮቻቸውና ውሳኔዎቻቸው ለዴሞክራሲና ነፃነት እየታገሉ ወይስ ዴሞክራሲና ነፃነትን እየታገሉ የሚል ጥያቄ የሚያስነሳ እየሆነ ነው።የተወሰኑትን እንዳስሳቸው።

በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲነት ዝርዝር ውስጥ ከሰፈሩት የተወሰኑት «ተቃዋሚ» የሚል ሰርተፍኬት ከመያዝ የዘለለ ተሳትፎ የሌላቸው መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው። ምርጫ ባርድ በቅርቡ ባቀረበው ጥሪ ይህ ገመና ተገልጧል። ሚና አላቸው ከተባለ የተቃውሞውን ጎራ አሃዝ በመጨመር «በኢትዮጵያ ውስጥ ይህን ያህል ተቃዋሚ ድርጅቶች አሉ» በማሰኘት የኢህአዴግን ምስል ማሳመር ነው። ግባቸው ይህም ሆነ ሌላ ዴሞክራሲውን ያጠወልገው፣ የህዝቡን ዘርፈ ብዙ ጥያቄዎች ከል ያለብሰው ካልሆነ ምንም አዎንታዊ ጎን አይኖረውም ብለን እናምናለን። እየፈፀሙ ያሉት ስህተት ያለውን አደጋ ቆም ብለው እንዲፈትሹም እንመክራለን።ይህ ተግባር ዴሞክራሲንና ነፃነትን እንደማፈን ይቆጠራልና።

ማንኛውም መብቱ በህግ ያልተገደበ ዜጋ በፖለቲካ ተሳትፎ ውስጥ የመካፈል መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የአንዳንዶቹ የ«ፖለቲካ ፓርቲዎች» አደረጃጀት መሰረታዊ ችግር ያለበት ይመስለናል። ይኸውም ፖለቲካ የራሱ ሳይንስ፣ ፍልስፍናና ጥበብ ያለው

ቢሆንም የአንዳንዶቹ የፖለቲካ ድርጅቶችና ፖለቲከኞች አካሄድ በዳበሳ የሆነበት አሳሳቢ ሁኔታ ይታያል፡፡ ከጠራ የፖለቲካ ፕሮግራም፣ ርዕዮተ ዓለምና የትግል ስልት ይልቅ የተዘበራረቀ፣ የዘፈቀደና የገደል ማሚቶነታቸውን የሚያጋልጥ የስሚ ስሚ ፖለቲካ ያራምዳሉ፡፡-ይህ ደግሞ የዴሞክራሲና የነፃነት ፀር ነው፡፡

የተቃውሞ ፖለቲካ ፓርቲዎች ሚና የገዢውን ፓርቲ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች መንቀፍ፣ አማራጭ ማቅረብና የመሳሰሉት ቢሆኑም ገዢውን ፓርቲ አወድሰው የማይጠግቡ ተቃዋሚ ነን ባዮችም እያየን ነው፡፡ ማወደስ መብት ሊሆን ይችላል፡፡ ደሞክራሲና ነፃነትን ለማምጣት ግን ውዳሴና እሺ ባይነት አዋራጆች እንጂ ገንቢዎች እንዳልሆኑ ማስታወስ ይገባል፡፡ ከእነዚህ መሰሎቹ ውጪ ያሉትና በአንፃራዊ ሁኔታ የተሻለ አደረጃጀትና ህዝባዊ ተቀባይነት ያላቸው ተብሎ የሚገመቱት ፓርቲዎችና ፖለቲከኞች ደግሞ በተለይ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ እየተከተሉ ያለው መስመር የነፃነት ታጋዮች ወይስ የነፃነት ጸር? የሚያሰኝ ሆኗል፡፡ የተቃውሞ ፖለቲካን ገንቢ ሚና ለመጫወት ያስችላቸዋል በሚል እምነት ሊያርሙ ይገባቸዋል ብለን ያሰብናቸውን ጥቂት ነጥቦች እናንሳ፡፡

የብሔራዊ እርቅ መድረክ ስለ መፍጠር ይሰብካሉ፡፡ በውስጣቸው በሚከሰቱ መጠነኛ ልዩነቶች ሳይቀር ግን ከመወያየት፣ ከመቻቻልና ልዩነቶቹን በድርጅታቸው መተዳደሪያ ደንብ ከመፍታት ይልቅ በከረረ ጥላቻ ውስጥ ወድቀው ሲወዛገቡ፣ ሲዘላለፉ እናያለን፡፡ ብሔራዊ እርቅ አስፈላጊ፣ ከፍተኛ የሞራልና የከበረ ስብዕናን ታሳቢ የሚያደርግ ከህዝብ ፍቅርና ከንፁህ አእምሮ የሚፈልቅ ሰፊ ስራ ነው፡፡ በየጥቃቅኗ ክስተት የሚናቆሩ ወገኖች እውን የሚያደርጉት አይደለምና አቋማቸውን ይመርምሩ ተግባር ያሳዩን እንላለን፡፡

ስለግልጽነትና ተጠያቂነት፣ ይሰብካሉ፡፡ ሙስናን ስለመዋጋት፣ ስለህግ የበላይነት፣ ስለሃቀኝነት፣ ለሌሎች ስለመታገል ይናገራሉ፡፡ አሰራራቸው ግልጽነት የጐደለው፣ ስልጣናቸው የማይገሰስና ተጠያቂነት የሌለበት፣ ለሌሎች መታገል ይቅርና ያለህግ ስርአት ታሰሩብን ስለሚሏቸው አባሎቻቸውና መሪዎቻቸውን በግልጽ ከመቃወም ይልቅ በአስተሳሰሩ ሂደት ላይ በማተኮር ራሳቸውን ነፃ ለማድረግ ይፍጨረጨራሉ፡፡ ከዚህ አልፎም «የራሳቸው ጉዳይ ነው» እስከማለት ይደርሳሉ፡፡ የነፃነት ታጋዮች ወይስ ነፃነትን ታጋዮች?

ተቃዋሚዎች ለግል የመገናኛ ብዙሃን ያላቸው ግንዛቤ ምን ይመስላል? የሚለውም አሳሳቢ ነው፡፡መንግስት ብንሆን የህግ ጥበቃ እናደርግላቸዋለን፣ ዜጎች ሃሳባቸውን የመግለጽና መረጃ የማግኘት መብታቸው ይከበራል... ቢሉም እኛ በፈለግነው መንገድ ካልፃፋችሁ፣ የማንፈልገውን ወገን ጽሁፍ በጋዜጣችሁ እንዳይወጣ ካላገዳችሁ፣ በአጠቃላይም የዘርፉ ተግባር መረጃ መስጠትና ማስተማር ሳይሆን የልሳንነት/ሎሌነት

ሚና እንዲኖረው የሚፈልጉ ያልበሰሉ «ነጻ አውጪዎች» ፓርቲዎች እያጋጠሙን ነው፡፡ ፕሬስ በባህርይው ከፍተኛ ነጻነትን፣ የሙያ ታማኝነትንና የሕዝባዊ ክብር መርህን በጥብቅ ይከተላል፡፡ ይህን ለማደናቀፍ መሞከርም በነፃነትና በዴሞክራሲ እሴቶች ላይ እንደተቃጣ ጥቃት እንቆጥረዋለን፡፡ በመጨረሻ ለህዝባችን ነፃነትና ዴሞክራሲ የሚታገሉትን ሁሉ በርቱ ተበራቱ እንላቸዋለን፡፡ ትግሉ በተቃራኒ ከሆነ ግን በታሪክ የሚያስወቅስ እንዲሁም «እሺ ባይና አንገት ደፊ» ትወልድ ለመፍጠር መማሰን ነውና ቆም ብላችሁ የውጤቱን አደገኛ መገለጫዎች አጢኑ ለማለት እንገደዳለን፡፡

**ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር !!!**

## Verbatim

«ከ25 አመት በኋላ ውብ ወደሆነው ወደዚህ ስፍራ ተመልሼ ሁላችሁንም በመልካም ጤንነት ላይ ሆናችሁ መመልከቴ ተዓምር ነው»

**ቦብ ጊልዶፍ**

**አርቲስትና በጎ አድራጊ**

**የ1977ቱን ረሐብ ለመግታት የአለማችን ታዋቂ አርቲስቶች የገቢ ማሰባሰቢያ ዝግጅት ያደረጉበትን 25ኛ አመት ለማክበር በሰሜን ኢትዮጵያ ኮረም ከተማ ተገኝቶ የተናገረው**

«ጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ ሂዱና እንደዚህ ጩኹ!»

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የአንድነት ፓርቲ አባል**

**«መርህ ይከበር» የሚሉ የአንድነት አባላት ከትናንት በስቲያ በኢምፔሪያል ሆቴል «ብርቱካን ሚዴቅሳ አሁንም መሪያችን ናት!» የሚል መፈክር ሲያሰሙ የሰጧቸው አስተያየት**

«ማንም አባል ወደ አንድነት ሲጋበዝ የምሳ ግብዣም ሆነ እንዲህ አይነት እንቅስቃሴ ተደርጐ አያውቅም፡፡ ... ከዚህ በፊት ባለስልጣኖች መሆናቸው እኮ የተለየ ጉዳይ አይደለም፡፡»

**ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም**

**አቶ ስዬ አብርሃና ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የአንድነት ፓርቲን መቀላቀል አስመልክተው በግዮን ሆቴል የምሳ ግብዣ ስለመደረጉ ተገቢነት ለአዲስ አድማስ የተናገሩት፡፡**

# ዜናዎች

## መንግስቱ ኃይለማርያም ታሪካዊ መጽሀፍ ፃፉ

የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም የ17 ዓመት ደም አፋሳሽ የስልጣን ቆይታቸውን የሚያወሳ አዲስ መጽሀፍ መፃፋቸውን የመጽሀፉን የአውራምባ ታይምስ ምንጮች ገለፁ፡፡

ከግንቦት 13 ቀን 1983 ዓ.ም ጀምሮ በዚምባብዌ ርዕሰ ከተማ ሐራሬ በጥገኝነት የሚገኙት ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም ስለ እርሳቸው በርካታ መፃህፍት በበርካታ ሰዎች ቢፃፉም እርሳቸው እንዴት ወደ ስልጣን እንደመጡ እንዲሁም የጋጠሟቸውን ፈተናዎች አስመልክተው ታሪካቸውን ለኢትዮጵያ ህዝብ በመጽሀፍ መልክ ይፋ የሚያደርጉበትን ጊዜ በርካታ ኢትዮጵያን በጉጉት ሲጠብቁት ቆይተዋል፡፡

ረቂቅ ጽሁፉን ያነበቡ ምንጮቻችን እንደገለፁት በኮ/ል መንግስቱ መጽሐፍ ውስጥ በተለይ ከ1966ቱ የአብዮቱ ፍንዳታ በኂላ የተከሰቱትን በአወዛጋቢነት የሚነሱ በርካታ ጉዳዮች ተካተውበታል፡፡ ኮሎኔሉ ራሳቸውን ለመከላከል የሞከሩ ያስመስልባቸዋል የተሰኙ ሁነቶች ላይ ሳይቀር የተሻለ መረጃ ያቀረቡበት ነው ተብሎላቸዋል፡፡ ኮ/ል መንግስቱ በ1953ቱ የመለዮ ለባሾች የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ባሉበት ጦር ውስጥ የነበራቸው ሚና እና እሱን ተከትሎ ይደርስባቸው የነበረው ተጽእኖ፣ የነበራቸው አቋምና ሰኔ 21 ቀን 1966 ዓ.ም በ4ኛ ክ/ጦር መምሪያ ከጦር ኃይሎች፣ ከፖሊስ ሰራዊትና ከብሔራዊ ጦር አስተባባሪ ኮሚቴ ተሰባስቦ ለነበረው ጦር የተመረጡበት ሁኔታ ተዳሷል፡፡ ከተለያዩ ክፍሎች የተሰባሰበው ጦር አላማ ስልጣን ለህዝብ አስረክቦ ወደየክፍሉ መመለስ ቢሆንም ከመስከረም 5 ቀን 1967 ጀምሮ የርዕሰ ብሔርነት ስልጣን የነበረው የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ጠቅላላ ጉባኤ ቢሆንም የካቲት 4 ቀን

1969 ዓ.ም ኮ/ሉ የደርጉ ሊቀ መንበር፣ የሚ/ሮች ም/ቤት ሰብሳቢና የጦር ኃይሎች ጠ/አዛዥ ሆነው የተመረጡበት ሂደት በጉዳዩ ዙርያ እስካሁን ከቀረቡት መድብሎች በተለየ ሁኔታ ያስነብቡናል:: ስንት ጊዜ የግድያ ሙከራ ተደረገባቸው? ይህስ የፈጠረባቸውን አንድምታ እንዴት ይገልፁታል?

የደርግ ሹማምንትና የፕሬዚዳንቱ 17 የስልጣን ዘመን፣ አገሪቱ የገባችበት ቀውስ እንዲሁም በንጉሰ-ነገስቱ ባለስልጣናት ላይ የተወሰደው ይግባኝ የማይጠየቅበት እርምጃ በገደምዳሜ ተንፀባርቋል:: ንጉሱን ማን ገደላቸው? የኮ/ል መንግስቱ ቤተሰባዊ ሁኔታ (አወዛጋቢው የትውልድ ሃረጋቸው) እና የመሳሰሉት ምላሽ ያገኛሉ ይላሉ የረቂቁ አንባቢዎች:: የየካቲት 25 ቀን 1967ቱ የመሬት ላራሹ አዋጅና ከዚያ ቀደም ሲል «ሶሻሊዝም» የአብዮቱ መመሪያ ሆኖ መታወጅ የነበራቸው መስተጋብር፣ ደርግ ስልጣኑን ለህዝብ ከማስረከብ ይልቅ የሙጥኝ ብሎ መቀጠሉ የሚነቀፍ ቢሆንም የደራሲ መንግስቱ ኃ/ማርያም መጽሐፍ የሚለው አለ:: በተለይም የመንግስት ለውጥን ተከትሎ በውስጥ የስልጣን ተጋሪ ለመሆን ከተቻለም ስልጣን ለመንጠቅ የሚፈልጉት ኃይሎች /ኢህአፓ በአዲስ አበባና በመላው አገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች ያደራጃቸው የፖለቲካና የመቺ ኃይል አባላት፣ የኢዲዩ በጎጃምና ጐንደር ላይ ኃይሉን ማደራጀት የሌሎችም በርካታ ንቅናቄዎች መፈጠር/ በውጭ ደግሞ የሶማሊያው ፕሬዝዳንት ጄኔራል መሐመድ ዚያድባሬ የወረራ ዝግጅት፣ የሱዳኑ መሪ ጃፋር ኤል ኑሜሪ ስልታዊ እንቅስቃሴ /የወረራ እቅድ/ የሻዕያና ጀብሃ መጠናከር፣ በደርግ ስልጣን ከማስረከብ ይልቅ የሙጥኝ ብሎ ለመቆየቱ የነበራቸው አንድምታ ተወስቷል:: ኢትዮጵያ የተቀላቀለችው የሶሻሊዝም ጎራ፣ የ1981ዱ የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ፣ የመጨረሻዎቹ የውጥረት አመታትና ኮ/ሉ ከአገር ወጥተው በዙምባብዌ መኖር የቀጠሉበት መንገድ «ምስጢሩ» ተዳሷል:: የኮ/ሉ የሐራሬ ኑሮ ምን ይመስላል? ምን እየሰሩ ይኖራሉ? ስለኢትዮጵያና ስለመንግስቷ ምን ይላሉ? የሚሉትና የመሳሰሉት በጉጉት ከሚጠበቁት ታሪካዊ ሁነቶች የተወሰኑት ናቸው::መጽሀፉም በአሁኑ ወቅት በህትመት ላይ የሚገኝ ሲሆን ከአንድ ወር በኋላ ለሽያጭ ይቀርባል ተብሎ ይጠበቃል::

# አንድነት ዶ/ር ነጋሶንና አቶ ስዬን አመራር አድርጐ መረጠ

## አውራምባ ታይምስ ጋዜጣን ይቅርታ ጠየቀ

አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ (አንድነት) ዛሬ በጽ/ቤቱ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ህገ መንግስታዊ መብቴ በህገ ወጥ ቡድኖች ተጥሷል ሲል አስታወቀ:: አንድነት

በመግለጫው እንዳስታወቀው መንግስት መብቴ ሲጣስ ዝም ብሎ መመልከቱ የአገሪቱ ህገ መንግስት የህዝቦችን ህልውና እንደማይጠብቅ የተመለከትንበት ነው ሲል አውግዟል:: በተያያዘ ዜና አንድነት ፓርቲ እሁድ ዕለት ለአባሎቹ በበተነው የምርጫ ፎርም መሠረት  በዕለቱ ከ8:00 እስከ 12:00 ሰዓት ፎርሞችን ሰብስቦ ባገኘው ውጤት ዶ/ር ነጋሶ  ጊዳዳንና አቶ ስዬ አብርሃን የፓርቲው የብሔራዊ ምክር ቤት አባል አድርጐ መምረጡን ይፋ አድርጓል::

አቶ ስዬ አብርሃ በበኩላቸው አንድነት እኔን በክብር ስለተቀበለኝ እግዜር ያክብርልኝ በማለት ለፓርቲው ምስጋናቸውን ያቀረቡ ሲሆን አንድነትን የመረጥኩት ህብረ-ብሄር አደረጃጀት ሥላለው ነው ብለዋል::

አንድነት ፓርቲ መገናኛ ብዙሃንን  በተመለከተ አንዳንዶቹ ከሙያ ስነ ምግባር ውጭ እየሰሩ ነው በሚል የወቀሰ ሲሆን ባለፈው ሐሙስ በጊዮን ሆቴል ባካሄደው ዝግጅት የአውራምባ ታይምስን ዘጋቢ ከፓርቲው  በቀረበለት ጥሪ መሰረት በስፍራው ቢገኝም አንዳንድ አባሎቻችን በጋዜጣው አዘጋገብ ላይ ያላቸውን ቅሬታ መሰረት አድርገው በዝግጅቱ እንዳይሳተፍ ከልክለዋል::» ሲሉ የፓርቲ ተ/ም/ሊቀመንበር ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው አውራምባ ታይምስ ጋዜጣን በይፋ ይቅርታ ጠይቀዋል::

ትናንት ለዶ/ር ነጋሶና ለስዬ አብርሃ የተለያዩ ጥያቄዎች ከጋዜጠኞች የቀረቡላቸው ሲሆን በየተራ ምላሽ ሰጥተዋል::

አቶ ስዬ ኢቴቪን እና ፖሊስ ኮሚሽንን «የኢትዮጵያ ፖሊስም ሆነ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እኔን የመጠበቅም ሆነ ድምፄን የማሰማት ግዴታ አለባቸው» ሲሉ ወቅሰዋል::

ኢ/ር ግዛቸው በበኩላቸው «ዝም አንልም የሚሉትን ህገ ወጥ ቡድኖች መንግስት አግዟቸዋል:: ለዚህም ማስረጃው ኢቴቪ ኢምፔሪያል ሆቴል የደረሰው ከጠዋቱ 1:30 ሰዓት ነው» ሲሉ ተናግረዋል::

ትናንት በኢምፔረያል ሆቴል አዳራሽ አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ (አንድነት) አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ጠርቶ የነበረ ቢሆንም ስብሰባው ሳይንሄድ ቀርቷል:: ስብሰባው የተጠራው ከጠዋቱ 2:00 ሰዓት ቢሆንም "መርህ ይከበር" የሚሉትና ከፓርቲ አባልነታችሁ ታግዳችኋል የተባሉት ወገኖች «እኛ መስራቾቹ ተሳታፊ ባልሆንበት ሁኔታ ስብሰባው የሚንሄድበት አግባብ የለም» በማለትና የተለያዩ መፈክሮችን በማሰማት ስብሰባው  እንዳይካሄድ አድርገዋል:: በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት መስራች አባላት ፓርቲው ሶስት አመት እስኪሞው ድረስ 327 መስራች አባሎች በሚደረገው እያንዳንዱ  ስብሰባ ላይ መሳተፍ መብታቸው እንደሆነ  ገልጸው ሆኖም ፓርቲው የጠራው 230ዎቹን ብቻ እንደሆነ ተናግረዋል:: በስራ አስፈፃሚው በኩል ያሉ አንዳንድ አባሎች በበኩላቸው "መርህ ይከበር" ባዮቹ በዲሲፕሊን ጉድለትና በድምጽ ብልጫ

የተባረሩ ስለሆነ በሰው ድግስ ላይ መጥተው ድግሱን ማበላሸት ህገ-ወጥ ድርጊት ነው ሲሉ ገልጸዋል:: ፐ/ር መስፍን የስራ አስፈጻሚውን አካሄድ «ቁጭ ብለን የሰቀልናቸውን ቆመን ማውረድ አቃተን» ሲሉ ተችተዋል::

እንደ ፐ/ር መስፍን ወ/ማሪያም ገለፃ ከሆነ በእለቱ የተጠራው አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አንድነት ሲመሰረት የወጣው መተዳደሪያ ደንብ ተሸሮ እነ አቶ ስዬ አብርሃንና ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳን ለመሾም ነው ካሉ በኋላ ለዚህም አቶ ስዬ አብርሃ አባል ሆነው ለመቀላቀል ያስቀመጡትን ቅድመ ሁኔታ "አዲስ አድማስ" ጋዜጣን ዋቢ በማድረግ ይናገራሉ:: በስራ አስፈፃሚው በኩል ያሉት ወገኖች በበኩላቸው ገርጂ አካባቢ ያለ ፖሊስ ጣቢያ ሄደው ጉዳዩን ቢያመለክቱም እንኳን ሌላ ተጨማሪ ፖሊስ ሊመድቡላቸው ቀርቶ በኢምፔሪያል ሆቴል የነበሩ ፖሊሶችም ከአካባቢው መጥፋታቸውን በቅሬታ ገልፀዋል:: የገርጂ አካባቢ ፖሊስ ጣቢያ አዛዦችም አባሎቻችሁን ሰብስቡ ተብለናል እና የምናውቀው ጉዳይ የለም በማለት ትብብራቸውን ተነፍገውና፣ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት ግን የሰላማዊ ሰልፍና ስብሰባ ማሳወቂያ ክፍል ህጋዊ ፈቃድ ተሰጥቶናል ብለዋል::

በዕለቱ መርህ ይከበር የሚሉት ወገኖች የተለያዩ መፈክሮች ያሰሙ ሲሆን «የአባላትን ድምጽ ያላከበረ አመራር የህዝብን ድምጽ ሊያከብር አይችልም»፣ «ብርቱካን ሚደቅሳ አሁንም መሪያችን ናት»፣ «አንድነት በኢትዮጵያ ብሄርተኝነት ላይ የተመሰረተ ፓርቲ ነው»፣ «በህገ ወጥ ጉባኤ የተወሰነው ውሳኔ ተቀባይነት የለውም»፣ «መሪያችንን አሳስሮ ፓርቲውን መንጠቅ አይቻልም»፣ «የአንድነት መርሆዎች አይሸራረፉም» የሚሉትና የመሳሰሉት ይገኙበታል:: በዕለቱ ጠቅላላ ጉባኤ በእነርሱ ምክንያት እንደተጠራ የሚነገርላቸው ግለሰቦች አቶ ስዬ አብርሃ እና ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የትዕይንቱ አካል አይደለንም በማለት ለብቻቸው ተቀምጠው ሲወያዩ ተስተውለዋል::

አንድነቶች የገርጂ ፖሊስ ጣቢያ አዛዦች መልስ አልሰጡንም በማለት ለጉዳዩ እልባት ለማግኘት ወደ ቦሌ ክ/ከተማ ፖሊስ ጣቢያ ቢሄዱም «እኛ በፖለቲካ ጉዳይ አይመለከተንም» ብለው መልሰውናል ብለዋል:: በዚህ ሁኔታ የሁለቱም ወገን አባሎች ኢምፔሪያል ሆቴል በር ላይ ሲጉላሉ ሰዓቱም ያለምንም ፋይዳ ነጐደ:: በስተመጨረሻም አንድነቶች ለአባላቶች የምርጫ ፎርም መሙያ ወረቀት ውጭ ላሉት በማደል ፎርሙን አስሞልተው ምርጫ ያካሄዱ ሲሆን ማንን እንደመረጡ ግን ይፋ አላደረጉም:: ጉዳዩን አስመልክተን አስተያየት እንዲሰጡን የጠየቅናቸው የአንድነት ፓርቲ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ ስለፖሊሶቹ ትብብር መንፈግና ስለ ስብሰባው መስተጓጐል ያለውን ሂደት ከመናገር በስተቀር "መርህ ይከበር" ስለሚሉትና ስለተያያዥ ጉዳዮች ከመናገር ተቆጥበዋል:: በመጨረሻም ስብሰባው እንደማይካሄድ ሲያውቁ ወደየቤታቸው ለመሄድ ከኢምፔሪያል ሆቴል ሲወጡ የነበሩት አቶ ስዬና ዶ/ር ነጋሶን ያዩት "መርህ

ይከበር" የሚሉት ወገኖች ፊት ለፊታቸው መፈክሮቻቸውን ይዘው ይጮኹ የነበረ ሲሆን በተለይም «ብርቱካን ሚደቅሳ አሁንም መሪያችን ናት» ሲሉ አቶ ስዬ «አዎ መሪያችን ናት» ሲሉ የተደመጡ ሲሆን ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ደግሞ «ሄዳችሁ ጠ/ሚ/ር ቢሮ እንደዚህ ጩኹ» በማለታቸው እዛው ተቃውሞ ገጥሟቸዋል::

በተያያዘ ዜና ከትናንት በስቲያ 11ኛው ወር የወ/ሪት ብርቱካን የእስር መታሰቢያ በአንድነት ለፍትህና ለደሞክራሲ ፓርቲ ጽ/ቤት ውስጥ የተከበረ ሲሆን "መርህ ይከበር" የሚሉት ወገኖች ደግሞ ከጽ/ቤቱ ውጭ በመሆን ሥነ ሥርዓቱን ማካሄዳቸው ታውቋል::

# በሀገራችን ከ1 ሚሊዮን በላይ ሰዎች በደማቸው ውስጥ ኤች አይ ቪ ይገኛል

## - የዓለም የኤድስ ቀን ዛሬ ይከበራል

የዓለም ጤና ድርጅት የመጀመሪያውን የዓለም ኤድስ ዘመቻ ካወጀበት እ.ኤ.አ ከ1988 ጀምሮ በየዓመቱ ዲሴምበር አንድ (ኅዳር 22) በመላው ዓለም «የዓለም ኤድስ ቀን» ይከበራል::ይህም በዛሬው ዕለት እየተከበረ ይገኛል::

ዘንድሮ የሚከበረው የዓለም ኤድስ ቀን «የፀረ ኤች አይ ቪ አገልግሎቶች ሁሉ አቀፍ ተደራሽነት እና ሰብዓዊ መብት» የሚል መሪ ቃልን መሰረት አድርጐ ነው::

መሪ ቃሉም ሲብራራ «የፀረ ኤች አይ ቪ አገልግሎቶች ሁሉ አቀፍ ተደራሽነት በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የምክርና የምርመራ አገልግሎት፣ ቫይረሱ በደማቸው ውስጥ ለሚገኝ ወገኖች የፀረ ኤድስ ሕክምና አቅርቦትን፣ ዘላቂነት ያለው ድጋፍና እንክብካቤ አገልግሎቶችን ያለምንም አድልዎና መድልኦ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ማዳረስን የሚያጠቃልል ሲሆን ሰብዓዊ መብት ግለሰቦች ሰው በመሆናቸው ብቻ የሚቀዳጇቸው ከክብራቸውና ከህልውናቸው ጋር የተያያዙ በማንም ሊጣሱ የማይችሉ ናቸው:: የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች በተለይም የፀረ ኤች አይ ቪ አገልግሎቶች ዜጐች ሊያገኙት የሚገባ መብት ነው:: ይህም እውን እንዲሆን ከመንግስት እና ከአስፈፃሚው አካላት እንዲሁም ከማህበረሰቡ የሚጠበቁ ነገሮች እንዳሉ ተገልጿል:: በአገራችን 1.116.216 የሚሆኑ ሰዎች ኤች አይ ቪ በደማቸው ውስጥ እንደሚገኝ፣

በኤድስ የሚሞቱ ሰዎች ደግሞ 44.751 እንደሚደርሱ ይገመታል፡፡ በዓመት በቫይረሱ የሚያዙ ሰዎች 131.145 ይደርሳሉ፡፡

ከቫይረሱ ጋር የሚወለዱ ህፃናት 14,140 እና በኤድስ ወላጆቻቸውን ያጡ ህፃናት ደግሞ 855.,720 ይገመታሉ፡፡

# አንድ ሴት የስምንት ቀን ህፃን ልጇን ገድላለች ተብላ ፍ/ቤት ቀረበች

የስምንት ቀን ህፃን ልጇን ሆን ብላ በማሰብ ጭካኔን በሚያሳይ መልኩ ገድላለች ተብላ የተጠረጠረች ወጣት በትናንትናው እለት በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 2ኛና 3ኛ ወንጀል ችሎት ፍ/ቤት ቀረበች፡፡

የአቃቤ ህግ የክስ ቻርጅ እንዳስረዳው ከሆነ ሀምሌ 9 ቀን 2001 ዓ.ም በልደታ ክ/ከተማ ቀበሌ 07/14 በሚገኘው የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የህፃናት ማዋለጃና ማቆያ ክፍል ውስጥ በጥሩ የጤና ሁኔታ ላይ ይገኝ የነበረው የስምንት ቀን ልጅ በተከሳሽ በልብስና በፎጣ ታፍኖ ተገድሏል ብሏል፡፡

ተከሳሽም ለችሎቱ «ልጄን በፎጣና ልብስ ጠቅልዬዋለሁ፡፡ በጊዜው ተሸፍኖ ስለነበረና አየር በማጣቱ ህይወቱ ሊያልፍ ችሏል፡፡ ልጄም ሞቶ የተገኘው አጠገቤ ነው፡፡ በወቅቱም አጠገቤ ማንም ሰው አልነበረም፡፡ ሆኖም ሆን ብዬና አስቤ ልጄን አፍኜ አልገደልኩትም፡፡ ወንጀሉንም አልፈጸምኩም፡፡» በማለት ቃሏን ሰጥታለች፡፡

ችሎቱም የአቃቤ ህግ ምስክሮች ቀርበው እንዲሰሙ ለታህሳስ 22 ቀን 2002 ዓ.ም ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

## <u>ኮሜንተሪ</u>

# የአንድነት ፓርቲ ለጨረታ

**በመስፍን ወ/ማርያም(ፕሮፌሰር)**

ኅዳር 17/2002 ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራው በግዮን ሆቴል ለሁለት ታላላቅ ሰዎች የምሳ ግብዣ አድርጓል፡፡ ይህ ሁነት የእንግዶቹን የትልቅነት መሠረት እንድንጠይቅ ያስገድደናል፡፡ እንደሚመስለኝ የሁለቱም ትልቅነት የሚመነጨው ጠቅላይ ሚኒስትር

መለስ ዜናዊ ከሰጣቸው ሹመት ነው። ሁለቱም ሰዎች ያንን የትልቅነታቸው መሠረት የነበረውን ሹመት በተለያየ መንገድ ጥለውት ሄደዋል፤ እንግዲህ ጥለውት በመጡት ሹመታቸው ላይ የተመሠረተ ትልቅነት ዛሬም አለ ከተባለ አቶ መለስ ከበላያቸው ቆሞ እንደፈጣሪ መታየት አለበት።- እኔ ሁለቱን ሰዎች እንደዚህ አላያቸውም።

ለእኔ የሁለቱ ሰዎች ትልቅነት የሚነሳው ከሹመታቸው ከተገላገሉ በኋላ ባሳዩት ቆራጥ አቅዋምና ሲያገለግሉት የነበረውን አገዛዝ በተቀናቃኝነት በሰላማዊ የፖለቲካ ትግል ፊት-ለፊት ለመጋጠም በመነሣታቸው ነው። ለእኔ ትልቅነታቸው ጥለውት የመጡት የትናንቱ ሹመታቸው ላይ ሳይሆን ዛሬ የያዙት የፖሊቲካ ተቀናቃኝነት አቅዋም ላይ ነው። ለእኔ ትልቅነታቸው ያለው ትናንት ለብሰውት የነበረው መንጦልያ ሳይሆን ዛሬ መንጦልያውን አውልቀው ራሳቸውን በራሳቸው ፈቃድ ለመለወጥ ባሳዩት ችሎታ ላይ ነው። ለእኔ ትልቅነታቸው ትናንት በሹመታቸው (በስልጣናቸው አልልም) በፈጸሙዋቸው ወይም ባልፈጸመዋቸው ሥራዎቻቸው ላይ ሳይሆን፣ በሹመታቸው ዘመን የስሕተትና የጥፋት ተባባሪዎች በመሆናቸው ተጸጽተው ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ይበጃል ላሉት ቃል ኪዳን አእምሮአቸውንና ልባቸውን መስጠታቸው ላይ ነው። ይህ ገና ያልተፈጸመ ራዕይ ነው፤ ስለዚህም ትልቅነታቸው የተከናወነ ሳይሆን የሚከናወን ተስፋ ነው፤ ለዚህ ተስፋ ያብቃቸው።

ዋናው ጉዳይ እነዚህ ሁለት ሰዎች በጥንቃቄ ተመርጠው ከተመለመሉ ጥቂት የአንድነት አባሎች ጋር በግዮን ሆቴል የተጋበዙበት ምክንያት ምንድን ነው? የሚል ነው። በአደባባይ እንደተነገረው ከሆነ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳና አቶ ስዬ አብርሃ የአንድነት ፓርቲ አባል ስለሆኑ ነው። የወንጌሉን ጠፍቶ የተገኘ በግ ምሳሌ ካላቀረቡ በቀር ምክንያቱ ይህ ብቻ ከሆነ ግብዣውም፣ ጋባዡም፣ ተጋባዦቹም ብዙ ችግሮች አሉባቸው፤

1. ዱሮ ፋኖዎች አንበሳ ሲገድሉ በድግስ ደስታቸውን እንደሚገልጹ ሁሉ ዛሬ እነ ኢንጂነር ግዛቸው ልዩ አባሎችን ለእጩነት በማቅረባቸው በግዮን ሆቴል ደገሱ። ተደርጎ አይታወቅም፤ ማናችንም፣ ጋባዡንና ተጋባዦቹን ጨምሮ፣ የፓርቲ አባል ስንሆን ድግስ ተደርጎ አያውቅም፤ እንዲያውም አንድነት እውቅናን ሲያገኝ መደገስና ለሕዝብ ማስተዋወቅ በሚያስፈልግበት ጊዜ አቶ አስቻለውም ሆነ ኢንጂነር ግዛቸው ለድግስ አላሰቡም ነበር።
2. የፓርቲ አባል መሆን ለእኔ እንደሚመስለኝ አዲስ ቃል ኪዳን መግባትና አዲስ ኃላፊነትንና መንፈሳዊ ግዴታን መቀበል ነው፤ ለአገርና ለወገን ሲባል በራስ ላይ ቀንበርን መጫን ነው፤ ስለዚህም ለመንፈሳዊ ግዴታ ቀንበርን በራስ ላይ ለመጫን በእዩልኝ-ስሙልኝ መጀመሩ የፖሊቲካ (የሕዝብ) ሥራም ቢሆን አዲሱ ቃል ኪዳናቸው ላይ ያጠላበታል።

3. ተደርጎ የማይታወቅ የመደለያ ግብዣ በአንድነት ፓርቲ ስም መደገስ ለእንግዶቹ ልዩ መብትን፣ ማለት እንደፓርቲ አባል የማይገባቸውን፣ ወይም ሌሎች የፓርቲ አባሎች ያላገኙትን ልዩ መብት መስጠት ነው፤ ይህንን ለአዲስ ገቢዎች የተሰጠውን ልዩ መብት ወደጸያፍነት የሚያስጠጋው ደግሞ የፓርቲው ፕሬዝዳንት ብርቱካን ሚዴቅሳ ከሕግ ውጭ ታስራ በምትገኝበት ጊዜ፣ በነዚያው በጋባዦቹ የሥልጣንና የገንዘብ ብልግና ብዙ መሥራች አባሎች ከፓርቲ ተባርረዋል በተባለበት ጊዜና የፓርቲው ዓላማዎችና ደንቦች ይከበሩ በሚሉ መሥራች አባሎችና የጉልበት አገዛዝን ለመትከል በሚፈልጉ የአመራር አባሎች መሀከል የውስጥ ትግል በተፋፋመበት ጊዜ መሆኑ ነው።

4. ከላይ በ(2) የተገለጸው ውጤት አለው። የአንድ ፓርቲ አባላትን እኩልነት ይሰርዛል፤ የዶ/ር ነጋሶና የአቶ ስዬ ትልቅነት ከፓርቲ አባልነታቸው ጋር ሲምታታና ውዥምብር ውስጥ ሲገባ ትልቅነታቸውም፣ የፓርቲ አባልነታቸውም መደብዘዝ ብቻ ሳይሆን ጥያቄዎችን ያስነሳል።

5. ዶ/ር ነጋሶና አቶ ስዬ ኢንጂነር ግዛቸው ያቀረበላቸው መሰላል ወደላይ የሚያወጣ ይሁን ወይስ ወደታች የሚወርድ ሳያመዛዝኑ ልዩ መብት ተቀባይ መሆናቸውና ከሌሎች አባሎች የተለዩ መስለው እንዲታዩ መፍቀዳቸው ቢያንስ ዓላማቸውን ጥያቄ ውስጥ ያስገባዋል፤ የሚያሳዝነው ደግሞ ጥያቄው ከሁለቱም ሰዎች ታሪክ ጋር ለመያያዝ የሚችል መሆኑ ነው፤ ሁለቱም ከነበሩበት የወጡት መንፈሳችንን አወረደብን በማለት ነው፤ ያሁኑስ?

6. ልዩ መብትን ማግኘት ልማድ ይሆናል፤ ዴሞክራሲን የሚሹ ሰዎች ሊያራምዱት የሚገባ አይደለም። ልዩ መብት የታየው በግብዣው ብቻ አይደለም። የአንድነትን መርህ በማስለወጥም ነው። ይህንን ከዚህ በታች እናየዋለን። አቶ ስዬ በግልጽ የተናገረውን ኢንጂነር ግዛቸው ለመደበቅና ለመሸፋፈን ሲጨነቅበት የሰነበተውን የአንድነትን መርህ የመለወጥ ዓማውን ያጋልጥበታል፤ ስሙን ጥላሸት ቀብቶ ለታሪክ የሚያበቃው ይህ ነው።

7. አንድነት ለቀጠራቸው ሰራተኞች ደመወዝ መክፈልና አስፈላጊ የፓርቲ ሥራዎችን ለማካሄድ ተስኖታል። የግዮን ሆቴሉ ግብዣ ከፓርቲው ውጪ ሆኖ ነው እንዳይባልበት ኢንጂነር ግዛቸው በቅድሚያ የአቶ አስቻለው ነው በማለት ተናገሩ ተባለ»። አቶ አስቻለው እንዲህ ያለ ግብዣ ለማድረግ የገንዘብ ችሎታ ካለው ፓርቲው ሲቸገር፣ ጽናት የሚለውን መጽሔት ለማሳተም መጠነኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች እየተቸገሩ ሲያዋጡ ምነው ዝም አለ? ለግብዣው ወጪውን የከፈለው አቶ አስቻለው ከሆነ ለምን የግል ግብዣ አድርጎ እሱ በራሱ ስም የፈለጋቸውን ሰዎች አይጋብዝም ነበር? ይህ ቢሆን ብዙ አከራካሪ

የሆኑ ጥያቄዎች አይነሱም ነበር። ጋባዡ አቶ አስቻለው፣ አስተናጋጁ ኢንጂነር ግዛቸው፣ ግብዣው በአንድነት ፓርቲ ስም፣ ተጋባዦቹ የተመለመሉ የአንድነት ፓርቲ አባላት መሆናቸው ግራ እንደሚያጋባ በጣም ግልጽ ነው።

የግዮኑ ድራማ ውሎ አድሮ በኢምፔሪያል ሆቴል ቀጠለ። እሁድ ኅዳር 20 እነኢንጂነር ግዛቸው በሕገ ወጥ መንገድ የአንድነት ፓርቲ ጠቅላላ ጉባኤ በኢምፔሪያል ሆቴል ጠርተው ስለነበር ዶ/ር ነጋሶና አቶ ስዬ በዚህ ስብሰባ ላይ ተጋብዘው በሆቴሉ ተገኝተዋል፤ እነሱ ገና የአንድነት አባል እንዳልሆኑና አባል የሚሆኑት ገና የአንድነት መርሆች ለነሱ እንደሚስማሙ ሆነው ከተለወጡ በኋላ ብቻ መሆኑን አቶ ስዬ ግልጽ አድርጎልናል (አዲስ አድማስ ኅዳር 19)፤ አቶ ስዬ ሌላም ዋና መረጃ ነግሮናል፤

*«በፕሮግራም ነክ ጉዳዮች ከአንድነት ፓርቲ ተቀዳሚ ም/ሊቀ መንበር ኢንጂነር ግዛቸው ሽፈራውና ከፓርቲው ዋ/ፀሐፊ አስራት ጣሴ ያደረግናቸው ተከታታይ ውይይቶች ተከትሎም አሁን ለድርጅቱ ጉባኤ በረቂቅነት በቀረበው ላይ ስምምነት ለመድረስ ችለናል፤ በመሆኑም ይህ ፕሮግራም የአንድነት ፕሮግራም ሆኖ ከፀደቀ ፓርቲውን በአባልነት ለመቀላቀል ወስኛለሁ።»*

እስቲ ቆም ብላችሁ አስቡት ብዙ ማሰብ የሚችሉ ሰዎችና የሕግ ባለሙያዎች ተሰብስበው ተወያይተውበትና ተከራክረውበት ያጸደቁትን ፕሮግራም ኢንጂነር ግዛቸው ና አቶ ዓሥራት በመደ-ነፍስ ለውጠው የአንድነት መለያ የሆነውን ፕሮግራም ለመሰረዝ በተለመደው የሴራ አሠራራቸው ሊያስወስኑ ስብሰባ ጠሩ፤ የጠቅላላ ጉባኤው የሥራ ዘመን ሦስት ዓመት ሲሆን የመጀመሪያዎቹን የጉባኤ አባላት በተለያዩ ምክንያቶች በማግለል እነሱ በገንዘብ፣ በምርጫ ተስፋና በሥልጣን ጫና የመለመሉዋቸውን ሰዎች አሰልፈው የአንድነትን ፕሮግራም ለዶ/ር ነጋሶና ለአቶ ስዬ እጅ መንሻ ለማድረግ አቅደው ነበር፤ ባለመብት የሆኑት ብዙ የጠቅላላ ጉባኤ አባሎች ሳይጋበዙ ሁለቱ እጩዎች ባለመብት ሆነው በስብሰባው ለመካፈል መጥተው ነበር።

በነዶ/ር ነጋሶ በኩል የሚያስገርመው ነገር እነሱ የሚፈልጉትን የፖለቲካ ፕሮግራም ቀርጸው የራሳቸውን ፓርቲ ለማቋቋም ለምን ተቸገሩና የተቋቋመና ሕዝብ ያወቀውን ፓርቲ ለማፍረስ ወይ ለማዳከም ምክንያት ለመሆን ተገደዱ? ለሁለቱም ሰዎች ያለኝ ቅንና በጎ አመለካከት ጥርጣሬ ውስጥ ገባብኝ። የቆመውን ከማፍረስ ሌላ መገንባት የተሻለ ይሆን ነበር። ከዚያም በላይ ገና የአባልነት ግዴታቸውን ሳያሙዋሉ በኢንጂነር ግዛቸውና በአቶ ዓሥራት ተጎትተው ምንም ሕጋዊ መብት በሌላቸው ስብሰባ ላይ ለመገኘት በኢምፔሪያል ሆቴል መገኘታቸው አንሶ እኛን ባለመብቶቹን ከአቋቋምነው ፓርቲ እንድንወጣ ጫና ለማድረግ መሞከራቸው በጭራሽ ከነዚህ ሰዎች የሚጠበቅ አልነበረም። ሚዛን የሌላቸው መስለው መታየታቸው በጣም ያሳዝናል።

ምን አይነት ስውር ኃይል ነው በስተጀርባ ቆሞ የሚገፋፋቸው? በእውነት የአንድነት መርሆዎች መለወጥ በዘንድሮው ምርጫ ኢህአዴግን ለማሸነፍ ይቻላል ተብሎ እንደሆነ ምኞታቸውና ተጨባጭ ሁኔታው የተደባለቀባቸው ሰዎች አሉ ማለት ነው፤ አንደኑት ከነመርሁና ከነደንቦቹ ተለውጦ ለጨረታ እንዲቀርብ እያዘጋጁት ያሉት ለአገርና ለወገን አስበው አይደለም:: ጉልበትና ገንዘብ ያላቸው ኃይሎች አንድነትን ከሕዝባዊ ዓላማው አጨናግፈው ለተወሰኑ ግለሰቦች ኑሮ ማሻሻያ ዘዴ ብቻ እንዲሆን ይፈልጋሉ:: ግለሰቦቹ ከዚህ ላይ ዓላማ እንደሌላቸው በጥቂት ጊዜ ውስጥ ምርጫው ሲደርስ ለመረዳት እንችላን:: ከበስተጀርባቸው ሆኖ የሚገፋፋቸው ኃይል ግን ዓላማው ገና በግልጽ አልታወቀም:: ስጋቴ ብዙ ጥፋቶች ተሰርተው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከፍተኛ ውዥንብር ውስጥ እንዳይገባ ነው:: ሀሳብንና እምነትን ማጥራትና ቆራጥ አቅዋም መያዝ የሚያስፈልግበት ጊዜ አሁን ነው::

## መጣጥፎች

# «መልካም ገፅታችን ቤቱ የት ነው... ምርቃና ወይስ ሞቅታ?»

***ይህ ንግግር የእኔ አይደለም::***

አቤ ቶኪቻው

abeto2007@yahoo.com

ወዳጄ ከዚህ በፊት ከአንድም ሁለት ጊዜ ስለ መልካም ገፅታችን በዚህ አምድ ላይ አውግተን እንደነበር አልዘነጋውትም:: ታድያ ዛሬም ይህንኑ ጉዳይ ሳነሳብዎ ይህ ሰው ነገር የመደጋገም አባዜ ተጠናወተውን? ብለው እንዳይጠረጥሩኝ:: እናስ...? ካሉኝ ነገሩ እንዲህ ነው:: እኔ እና ሌሎች የሀገራችን መልካም ገፅታ የሚያሳስበን ሰዎች በምንም አይነት አስከፊ ሁኔታ ውስጥ ብንገኝም እንኳ ስለ መልካም ገፅታችን ተናግረን አንጠግብም:: ሁሌም መልካሙን ብቻ እናወራለን:: መልካሙን ብቻ እናበስራለን:: መልካሙን ብቻ እንዘምራለን:: ይህ ከአንድ ለመንግስቱ እና እና ለእርስቱ፣ ለሀገሩ እና ለትዳሩ፣ ከሚጨነቅ ልማታዊ ግለሰብ የሚጠበቅ ልማታዊ ስራ ነው:: እናም በተገኘው መድረክ ላይ ሁሉ ስለ መልካም ገፅታ እናወራለን:: በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የሀገራችንን ጥጋብ እንሰብካለን:: ይህ ያልተዋጠላቸው አንዳንዶች ግን መልካሙን ንግግር በክፋት ተረጎሙት::

እንዲህም አሉን «ይቺ መልካም ገፅታዋን የምታስተዋውቁላት የጥጋብ ሀገር፣ የምቾት ቀዬ የዴሞክራሲ ሰፈር፣ የድሎት ሜዳ የምትሏት ምድር ከወዴት አለች? የመልካም ገፅታችንስ ቤቱ የት ነው?» ሲሉ ጠየቁን።
እስቲ በሞቴ «መልካም ገፅታችን ቤቱ የት ነው?» ብሎ ጥያቄ ምን ይሉት ጥያቄ ነው? መቼም ጆሮ አልሰማ አይልም እና እኒህ ለመልካም ገፅታችን መልካም አይን የሌላቸው ግለሰቦች እንዲህ ሲጠራጠሩ ሰማሁኝ። «መልካም ገፅታችን ቤቱ የት ነው... ምርቃና ወይስ ሞቅታ?»
ቀጥሎ ምርቃና እና ሞቅታን ለማታውቋቸው ወይም በደህናው ግዜ ታውቋቸው ለነበረ እና በአሁኑ ወቅት ለዘነጋችኋቸው ወዳጆቼ እንደሚከተለው አስታውሳለሁኝ።
ምርቃና ማለት ጫት የተባለውን ገንዘብ አስውጪ ለምለም ነገር በመግዛት እና በመቃም የሚመጣ ሃሴት ሲሆን የወደፊት ምኞትን አሁን አጠገብ ያለ አስመስሎ የማየት ልዩ ችሎታን ያጎናፅፋል። በምርቃና ጊዜ በርካቶች መልካምን ብቻ ያስባሉ። ስለመልካም ብቻ ያወጋሉ። ምርቃና የሰፈፈበት ቤት ችግር አይወራም። በዚህ ጥጋብ እንጂ ጉስቁልና ቦታው አይደለም። በዚህ ነገሮች ሁሉ መፍትሄ አላቸው። በምርቃና ቤት፤ ሁሉም ባለ ርዚቅ ሁሉም ባለፀጋ ነው።
ሞቅታ ደግሞ ያላበው ቢራ ወይም በረዶ የተጨመረበት ውስኪ (አሰይ! አጠራሩ ራሱ እንዴት ያምራል?) አልያም ለመዋኛ በሚበቃ ብርጭቆ የተቀዳ ጃምቦ ደጋግመው ከጠጡ በኋላ የሚገኝ የደስታ ጥግ ነው። ሞቅ ያለው ሰው የሞቅታው ምሽት ባይነጋ፣ ሞቅ እንዳለው ዘላለም ቢሆን ምርጫው ነው። ሞቅ ላለው ሰው ዙሪያው በችግር ቢታጠር የሚያይበት አይን የለውም። ዳንስ ጭፈራ ሳቅ እና ጨዋታ ሞቅ ያለው ሰው መገለጫዎች ናቸው።
ወዳጄ ለመሆኑ እንዴት ሰንብተውልኛል? ጤናዎ እንደምን ባለ ሁኔታ ላይ ይገኛል? ግራ ቀኙ ሀገር ቀየው አማን ውሎ ማደሩ ጥርጥር የለውም። የእኔም ያም ፀሎት ለዚሁ ነውና ሁሌም ደህና ነኝ ይበሉኝ ወዳጄ። እርስዎ ደህና ባይሆኑም እንኳ ደህና ነኝ ባሉ ጊዜ የሀገርዎን መልካም ገፅታ እየገነቡ እንደሆነ ላስታውስዎ እወዳለሁኝ።
በነገራችን ላይ ስለ መልካም ገፅታ ግንባታ ሲወራ የእኛ ቤተሰብ ግንባር ቀደሙን ቦታ ሳይዝ አይቀርም ብዬ እጠረጥራለሁኝ። ዛሬ ሳይሆን ድሮ የኢትዮጵያ ህዳሴ ማብሰርም ሆነ ማስከር ሳይጀመር በፊት ገና ያኔ የመልካም ገፅታችን ግንባታም ሆነ የኮንዶሚኒየም ቤቶች ግንባታ ሳይጧጧፍ በፊት ያኔ እኛ ቤት ግን ለቤተሰባችን መልካም ገፅታ ግንባታ ትልቅ ቦታ ይሰጠው ነበር። መልካም ገፅታችን ከሚገነባባቸው መንገዶች አንዱ የሚከተለው ነው።
እንግዳ በቤታችን ይመጣል። የዛን ግዜን እንግዳ ሲቀበሉት እንደዛሬ አልነበረም እና «አረፍ በል» ብላ፣ ጠጣ፣ ከትኩሱ፣ ቀዝቃዛው፣ እየተባለ ይጋበዝ ነበር። ድሮ እንኳንስ

በዕቅድ ለመጣ እንግዳ ይቅርና በድንገት ለደረሰ እንግዳ እንኳ «ምን ይታረድ? ምን ይጠበስ? ምን ይቀቀል? ማለት ደንብ ነበር። እኛ ቤት ሲሆን ደግሞ ባስ ይላል መሰል እንግዳ ከመጣ በልቶ ጠጥቶ ጠግቦ ካልሔደ በስተቀር እኛ የቤተሰቡ አባላት ምግብ በአፋችን አይዞርም።

በእድሜ ልጅ የሆነው የቤተሰቡ አባላት እንግዳ ፊት ለመቅረብ የተለያዩ ቅድመ ሁኔታዎች ይጣሉብን ነበር። ፊታችንን መታጠብ፣ ቫዝሊን መቀባት፣ የታጠበ ልብስ መልበስ በአጠቃላይ እንግዳው ባየን ግዜ «እንዴት የሚያማምሩ ልጆች ናቸው?» እንዲል ማድረግ  እንዲሁም እንግዳው «ይቺን ላጉርስህ» ብሎ ከሚበላው የመጋበዝ ዝንባሌ ካሳየ «የለም ጠግቤያለሁኝ» ብሎ ማለት። (ለነገሩ ይሄንን እንኳ እናታችን የምትሰራው ስራ ነው። እንግዳው ወዘናችን ከተቀባነው ቫዝሊን እንጂ ከምቾት የተነሳ አለመሆኑን ሲጠረጥር ገና «አፈር በበላሁኝ ና እስቲ ይቺን ላጉርስህ» ሲል እናታችን «አረ በቃው አሁን እኮ ጓዳ ብላ አትብላ ጭቅጭቅ ነበር። የእኔ ልጆች ምግብ አይበሉ ይኸው ወሬ ለምደው ወደዚህ እየሮጡ መጡ» ትላለች እውነቱን ለመናገር ግን በጓዳ ውስጥ ጭቅጭቅ  ከነበረ ጭቅጭቁ ምግብ ስጪን «የለም እንግዳ ሳይሸኝ አትበሉም» የሚል መሆን አለበት።) ነገር ግን ለቤተሰቡ መልካም ገፅታ ግንባታ ሲባል ግን እናታችን የእኛን ጥጋብ ለእንግዳው ብቻ ሳይሆን ጎረቤት እስኪሰማ ድምፀዋን ከፍ አድርጋ ትመሰክራለች። በዚህ አይነት መልኩ ያደግሁት እኔም የእናቴ ልጅ ዛሬ የሀገሬን መልካም ገፅታ ለመገንባት እየተጋሁኝ እገኛለሁኝ። ሀገሬ የተለያዩ አለም አቀፍ እና አህጉር አቀፍ ዝግጅቶችን በምታስተናግድባቸው ዕለቶች ልብ ብላችሁ ብትመለከቱኝ ቫዝሊኔን ተቀብቼ የክት ልብሴን ለብሼ ባልበላም እያገሳሁኝ ደስ ባይለኝም እየሳቅኩኝ የሀገሬን መልካም ገፅታ ንቁ ተሳትፎ አደርጋለሁኝ።

በከተማችን አዲስ አበባ የህንፃ ግንባታው በየአቅጣጫው እየተጣደፈ ይገኛል። («በስምንተኛው ሺህ ቤተ ሰሪ ይበዛል የሚኖርበት ግን የለም» እያላችሁ ልማቱን የምታሽሟጥጡ አንዳንድ ግለሰቦች «አረ ተዉ ባትነኩን ምናለበት እባካችሁ ሰዎች ስራዬን ልስራበት» የሚለውን ዜማ ልንጋብዛቹ እንገደዳለን) የሆነ ሆኖ የህንፃ ግንባታው ከኮንዶሚኒየም ቤቶች እስከ ሪል እስቴት ድረስ በስፋት እየተገነባ ይገኛል። ታድያ ከህንፃ ግንባታው ጎን ለጎን የመልካም ገፅታ ግንባታው ካልተጧጧፈ በቀር ልማቱ ምሉዕ ሊሆን አይችልም እንደውም ዋናው ግንባታ ሲሚንቶ ተወደደ የማይባልበት አሸዋ ጠፋ የማይባልበት ግንባታ መልካም ገፅታን መገንባት ነው።

የመልካም ገፅታን ጥቅም አብጠርጥረን የተረዳነው እኔ፣ አዲስ ዘመን ጋዜጣ፣ እና ኢቲቪ መልካም ገፅታ ግንባታ ላይ ተጠምደን ይኸው ሀገራችን ማር የሚዘንብባት፣ ዴሞክራሲ እንደዳቦ የሚገመጥባት፣ መልካም አስተዳደር እንደጃንቦ የሚጨለጥባት፣መሪዎቿ ከተቃዋሚዎች ጋር እንደ ቤተዘመድ የሚተቃቀፉባት፣

ገበሬዎቿ ከሀገር አልፌው የውጪ ገበያ ፍላጎት የሚያሟሉባት፣ የጥጋብ ሀገር ደስታ ምድር እንደሆነች እየሰበክን ባለንበት በዚህ ወቅት ታድያ አንዳንዶች እንዲህ አጉረመረሙ «የምትናገሩለት መልካም ገፅታችን ቤቱ ከየት ነው ከምርቃና ነው ወይስ ከሞቅታ?» ሲሉ ጠየቁን እነደምን እንዲህ ይባላል? ባልናቸውም ጊዜ «አንድ ሰው በሞቅታ ውስጥ ካልሆነ አልያም የምርቃና አለም ውስጥ ካልገባ በስተቀር እንደምን ዘላለሙን ፌሽታ ብቻ ያወራል? ብለው ይጠይቁ እና «ስለ እውነት ስለ እውነት እንላለን እናንተ የምትሉት አይነት ሃገር በዲቪ እንዜድ እንደሆነ እንጂ አሁን ግን አልተፈጠረም!» ሲሉ የለየለት ጨለምተኛ ንግግር ይናገራሉ።

ያሉትን ይበሉ እንጂ እኔ አዲስ ዘመን ጋዜጣ እና ኢቲቪ ግን ዘላለም ጥጋብ ዘላለም ምቾት ዘላለም ድሎት እያወራን እንቀጥላለን! ምክንያቱም እኛ ልማታዊ ሰራተኞች ነን። እኛ ከሁሉ በላይ የሚያስጨንቀን ሀገሪቱ ቫዝሊኗን ተቀባብታ በሌሎች ዘንድ ወዘናዋ ሞገስ እንዲያገኝ ነው። እኛ ««ታላቁ ሩጫ ብሶት መግለጫ...» አንልም «በታላቁ ሩጫ ታየ ማሳለጫ» እንላለን እንጂ።

በመጨረሻም :- 1

ባለፈው ሳምንት ውስጥ ነው መሰለኝ (አንድ ወዳጄ «በመሰለኝ አታውራ» እያሉ ሲወቅሱኝ ነበር ታድያ ሲመስለኝ ምን ልበል ወዳጄ?) እናም ይመስለኛል ባለፈው ሳምንት ውስጥ ግፋ ቢል ደግሞ ከዛም አንድ ሳምንት በፊት ሬድዮ ፋና የምስረታ በዓሉን ያከብር ነበር አሉ። ታድያልዎ በዚህ የምስረታ በዓል ላይ አንድ «የተቃዋሚ» ፓርቲ መሪ የሆኑ ግለሰብ (ግለሰቡ በተለይ ከገዢው ፓርቲ ይልቅ ተቃዋሚዎችን በመቃወም ይታወቃሉ።) እናም እኒህ ሰው አንድ ጥናታዊ ፅሁፍ እንዲያቀርቡ ተጋብዘው ሳይገኙ ቀሩ አሉ። ታድያ አንዳንድ አግቦ ተናጋሪዎች «ምነው ከእንዲህ ያለ ቤተዘመድ ጉባኤ እንዴት ይቀራሉ?» ብለው ሲያሽሟጥጡ አልከረሙም መሰልዎ! ይባስ ብለው የፖለቲካ ፓርቲ መሪው ለአንድ ጋዜጣ «ጥናታዊ ፅሁፉን እንዳቀርብ የተሰጠኝ አንድ ቀን የማይሞላ ጊዜ ነው» ብለው የተናገሩትን አንብበው «ታድያ እኮ ያውቀዋል ቤተኛ ነው ብዙም ጥናት ማድረግ አያስፈልገውም ተብሎ ነው» እያሉ ሲያሽ ሚጥጡ እኛም ስንመክር ከረምን እልዎታለሁኝ። (በነገራችን ላይ ሬድዮ ፋናዎች እንኳን ለምስረታ በዓላችሁ በሰላም አደረሳችሁ አሪፍ አሪፍ ፕሮግራሞች አሏችሁ እና በርቱ!)

በመጨረሻም 2:-

አሁን እንኳ እርግጠኛ ነኝ ባለፈው ሳምንት ውስጥ ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ እና አቶ ስዬ አብርሃ «አንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትህ» ፓርቲን በይፋ መቀላቀላቸው ተሰምቷል። በእውነት ለአንድነት ፓርቲ ብቻ ሳይሆን ለአንድነት መንፈስ ራሱ እነዚህ እድሜያቸውን በብሔር ፓርቲ እና ግንባር ያሳለፉ ሰዎች ሀገራዊ ራዕይ ሰንቀው መነሳታቸው ትልቅ ደስታ ነው። መሪውን ብርቱካን ሚዴቅሳን «የተበላው» አንድነት ፓርቲ እኒህን አዲስ

እንግዶች አቀባበል ባደረገበት ዕለት ታድያ የአውራምባ ታይምስ ዘጋቢው ወዳጃችን ለዘገባ ወደዝግጅቱ አምርቶ ነበር:: ሆኖም አዘጋጆቹ «አልጠራንህም ተመለስ» ብለው ከበር መለሱት:: አሉ:: በዚህ ጊዜ በእውነት ክፍት አለኝ እና እነዚህ ሰዎች መንግስት ሳይሆኑ እንዲህ ካደረጉ መንግስት ሲሆኑ እንዴት ሊሆኑ ነው? ስል ሃሳብ ገብቶኝ ባለበት ሰዓት አንዱ ወዳጄ «አትፍረድባቸው...» አለኝ እንዴት? ብለው «አንድ አንዶቹ ፖለቲከኞቻችን ካርታ ቤታቸውን ዘግተው ቀጥታ ወደፖለቲካው የመጡ ስለሆኑ እያደር የካርታ ቤታቸው ባህሪ እስኪለቃቸው መታገስ ነው እንጂ መፍረድ አይገባም» አለኝ:: (እኔ የለሁበትም)

ወዳጄ ይበሉ ያሰናብቱኝ እና ሳምንት እንገናኝ::

አማን ያሰንብተን!

# ስዬ ወደ አንድነት-
# የገነቡትን ለማፍረስ ወይስ ያልዘሩትን ለማጨድ ?

**በዳዊት ከበደ**

የቀድሞው የኢፌዲሪ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳና የቀድሞው መከላከያ ሚኒስትር አቶ ስዬ አብርሃ አንድነት ፓርቲን በይፋ መቀላቀላቸው የሰሞኑ መነጋገሪያ አጀንዳ ሆኗል:: ባለፈው ሐሙስ አቶ ስዬና ዶ/ር ነጋሶ አንድነት ፓርቲን በይፋ የመቀላቀላቸውን ዜና በውጭ ድረገጾች ሲቀርብ ኢትዮጵያዊያን በዜናው ላይ የተለያዩ አስተያየቶች ሰጥተዋል:: በኤሊያስ ክፍሌ የሚመራው «ኢትዮጵያን ሪቪው» ድረገጽ ለምርጫ እየተዘጋጁ ያሉ የኢትዮጵያ ፓርቲዎች በሁለት ጎራ ይከፍላቸዋል:: በሁለቱም ጎራ ያሉ ተፋላሚዎችም ኢህአዴግ መሆናቸውን ገልጾ በሁለት ኢህአዴግ መካከል የሚካሄድ ምርጫ ነው ብሎታል:: ምክንያቱን ሲያስቀምጥ በአንድ በኩል መኢአድን ያቀፈውና በስልጣን ላይ ያለው ኢህአዴግ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የቀድሞ ኢህአዴግ አመራሮችን ያቀፈው አንድነት/መድረክ ነው ይላል::

«ናዝሬት» የተሰኘው ድረገጽ በበኩሉ በመላው ዓለም የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን በዚህ ዙሪያ አስተያየት እንዲሰጡ ባቀረበው ጥሪ መሰረት በመቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊያን አስተያየት ሰጥተዋል:: ከጥቂቶች በስተቀር የበርካታዎቹ አስተያየት አሉታዊ ነበር:: በተለይ አንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች በ1985 ዓ.ም ተገደሉትን የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን የበደኖ ጭፍጨፋ አስመልክቶ ያሉትን ጥርጣሬዎች በማንሳት ጭምር እነ ስዬን «ከህግ ተጠያቂነት አታመልጡም» የሚል አስተያየት አስፍረዋል:: በአንጻሩ ደግሞ ደሳለኝ አስፋው የተባሉ ጸሐፊ በ«ኢትዮፖለቲክስ» ድረገጽ ላይ ባሰፈሩት ጽሁፍ «በጎ ጅምር» ሲሉ እርምጃውን አድንቀዋል:: በኢትዮፎረም

ድረገጽ ላይ አስተያየት ከሰጡ ኢትዮጵያዊያን መካከልም ብዙዎች ለግለሰቦቹ ድጋፋቸውን ሰጥተዋል።

ምርጫው እየተቃረበ እንደመሆኑ «መድረክ» በአንድ የመወዳደሪያ ምልክት ሁለቱም ግለሰቦችን አቅፎ ምርጫ ውስጥ የሚገባ ከሆነ፤ሰዎቹ ከመድረክ አባል ፓርቲዎች ውስጥ  አንዱን መርጠው እንደሚቀላቀሉ ሲጠበቅ ነበር። በብዙዎች ዘንድ የነበረው ግምት ዶ/ር ነጋሶ ኦፌዴንን አልያም ኦብኮን አቶ ስዬ ደግሞ ዓረና ፓርቲን (በ1993 ዓ.ም. ከአቶ ስዬ ጋር ህወሓትን የተሰናበቱ ጓዶቻቸው የመሰረቱት ፓርቲ) ይቀላቀላሉ የሚል ሰፊ መላምት ነበር። ምክንያቱም ሁለቱም ከቀድሞ ጓዶቻቸው ጋር በብሔር ላይ የተመሰረተ ፖለቲካ በአገሪቱ ስር እንዲሰድ ዓይነተኛ ሚና የተጫወቱ እንደመሆናቸው ከዚህ ማዕቀፍ ወጥተው ህብረ ብሔራዊ ፓርቲ ውስጥ ገብቶ ደጋፊን ማሰባሰብ «ያልዘሩትን እንደማጨድ» ይቆጠራል። እንደውም ቀላል በማይባሉ አክራሪ ብሄርተኛ ደጋፊዎቻቸው ዘንድ በ«ከሃዲነት» ሊፈረጁ ይችላሉ። የሚሉ አስተያየት ሰጪዎችም አሉ። ለመግቢያ ያህል ይህን ካልኩኝ ወደ ዋናው ርዕሰ ጉዳይ ልግባ።

ሚያዚያ 15 ቀን 2000 ዓ.ም ረፋዱ ላይ አቶ ስዬ አብርሃ ስልክ ደውለው «ጊዜ ካለህ እቤት መጥተህ በአንዳንድ ጉዳዮች ላይ እንዲሁ በግል እንድንወያይ ፈልጌ ነበር» አሉኝ። እኔም ደስተኛ መሆኔን ገልጬ ወደ መኖሪያ ቤታቸው አቀናሁኝ። ስለአገራችን ወቅታዊ  የፖለቲካ ሁኔታ በወቅቱ  ስለነበረው የተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ እንዲሁም ስለ ገዥው  ፓርቲ አንዳንድ ሐሳቦች አንስተን ተወያየን። ዛሬ ላይ ሆኜ ስለያኔው ውይይታችን ሳስብ  በአንዳንድ ነገሮች ላይ ግራ መጋባቴ አልቀረም። ብዙ አንባቢያን እንደምታስታውሱት በወቅቱ የነበረው የተቃዋሚዎች  እንቅስቃሴ የጠራ መስመር አልያዘም ነበር። እነ ወ/ሪት ብርቱካን አንድነትን አልመሰረቱም፤ እነ ኢ/ር ኃይሉ ሻውልም በይፋ ወደ መኢአድ አልተመለሱም፤ ዶ/ር  ብርሀኑ በሰላማዊ ትግል ተስፋ መቁረጣቸው ይገለጽ እንጂ ግንቦት 7ን አልመሰረቱም ነበር። ሁሉም ግን በየፊናቸው በሚያደርጉት እንቅስቃሴ «የቀድሞ ቅንጅት አመራሮች» እየተባሉ ነበር የሚጠሩት። ከአቶ ስዬ ጋር በነዚህና በሌሎች ጉዳዮች ዙሪያ ሰፋ ባለ ሁኔታ ሀሳብ ከተለዋወጥን በኋላ አቶ ስዬ «ምናልባት ከዶ/ር ብርሃኑ ጋር መግባባት ይቻል ይሆናል። እዚህ ካሉ ሌሎች ተቃዋሚዎች ጋር አብሮ መስራት ግን የማይታሰብ ነው» አሉ። ለዚህ ደግሞ አንድ ቀላል ምክንያት ማንሳት ይቻላል። የመጀመሪያው ምክንያት አቶ ስዬ ይደግፈኛል ብለው የሚተማመኑበት የትግራይ ህዝብ በ1997 ዓ.ም ምርጫ ለኢህአዴግ ሙሉ ድጋፍ የሰጠ ከመሆኑም በላይ ገዢው ፓርቲ ቅንጅትን ከ«ኢንተርሀምዌ» ጋር በማያያዝ ትግራይ ውስጥ ሰፊ ቅስቀሳ ማካሄዱ የሚዘነጋ አይደለም። ከዚህ አንጻር ከቀድሞ ቅንጅት አመራሮች ጋር ጥምረት ፈጥሮ ትግራይ ውስጥ ድጋፍ ለማሰባሰብ መሞከር ከባድ እንደሚሆን በውይይታችን መሀል አቶ ስዬ አልሸሸጉም። እንደውም «አሜሪካ ውስጥ

ከዶ/ር ብርሃኑ ጋር ፖለቲካዊ ውይይት አደረገ ተብሎ የተናፈሰው ወሬ ገዢው ፓርቲ ሆን ብሎ የነዛውና "ስዬ ቅንጅት ሆነ" ተብሎ በትግራይ ህዝብ ዘንድ እንዲጠላ ለማድረግ ነው» በማለት መግለጫ መስጠታቸው አይዘነጋም:: ሁለተኛው የአቶ ስዬ ነጥብ የተቃዋሚዎች መንደር «የንትርክ አውድማ» የመሆኑ ጉዳይ ነበር:: በዚህ ዙሪያ እስከቅርብ ጊዜ ድረስ ተመሳሳይ አቋም እንደነበራቸው ግልጽ ነው:: በዚህ አመት መጀመሪያ ላይ ከአንድነት ወጣቶች የቀረበላቸው ድንገተኛ የአባልነት ጥያቄ «አንድነት ያልተሰራ ቤት ነው» በማለት ጥያቄውን ውድቅ ማድረጋቸው አይዘነጋም:: ታዲያ ያ ያልተሰራ ቤት ከመቼው ተሰርቶ ለአቶ ስዬ ዝግጁ ሆነ? የሚል ጥያቄ ያጭራል::

እንደ አንድ ዜጋ ሁለቱም ግለሰቦች አንድነት ፓርቲን መቀላቀላቸው እደግፋለሁ:: ከዛ ባሻገር ግን ዶ/ር ነጋሶ የሰሩት አቶ ስዬ ግን «በመቃብሬ ላይ» የሚሉት አንድ ወሳኝ የቤት ስራ ያለ ይመስለኛል:: እሱም የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ የመጠየቅ ጉዳይ ነው:: ጠ/ሚ መለስ ባለፈው አመት በአገሪቱ የተከሰተውና መጠነ ሰፊ ኢኮኖሚያዊ ምስቅልቅል ያስከተለው የኤሌክትሪክ መቋረጥ አስመልክቶ የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ እንዲጠይቁ በፓርላማ ጥያቄ ሲቀርብላቸው «ድህነት ይቅርታ ይጠይቅ እንጂ አላደርገውም» አሉ:: የምትመራውን ህዝብ ይቅርታ መጠየቅ የአክብሮት እንጂ የሽንፈት መገለጫ አይደለም:: ለኢህአዴግ አመራሮች ግን ይቅርታ መጠየቅ የአለም ፍፃሜ ነው:: የአቶ ስዬ ይቅርታ አልጠይቅም ማለት የኢህአዴግ አክራሪነት ባህሪይ እስካሁን እንዳልለቀቃቸው ከማሳየት ውጪ ሌላ መልእክት የለውም:: ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) በ1967 ዓ.ም የሽምቅ ውጊያ ከጀመረ ከአንድ አመት በኋላ ትግሉን የተቀላቀሉት አቶ ስዬ እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ በከፍተኛ ወታደራዊ አመራርነት ደረጃ ጥሩ አዋጊና ተዋጊ እንደነበሩ ይነገርላቸዋል:: ከ1983 ዓ.ም እስከ 1993 ዓ.ም ድረስ ለ10 ዓመት ያህል በተለያየ የመንግስትና የፓርቲ ኃላፊነት ላይ አገልግለዋል:: መከላከያ ሚኒስትር፤የኢትዮጵያ አየር መንገድ የቦርድ ሊቀመንበር፣ የፓርላማ አባል፣ በአሁኑ ወቅት በቀዳማይት እመቤት አዜብ መስፍን የሚመራው ኤፌርት የቀድሞ ዳይሬክተር፣የህወሓት ፖሊት ቢሮ አባል እንዲሁም የበርካታ ሹመቶች ባለቤት ሆነው «ጦርነትን መፍጠር እንችላለን» እስከማለት የደረሱት ሰውዬ «ንጹህ ሰው ነኝ ይቅርታም አልጠይቅም» ሲሉ አሳማኝ አልመሰለኝም::

በሌላ በኩል ደግሞ ዶ/ር ነጋሶ ባለፈው ሐሙስ የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ ጠይቀዋል:: ዶ/ር ነጋሶ «ሳላውቅ ተታልዬ መጠቀሚያ ሆንኩ» ሲሉ ብዙ ጊዜ ይደመጣል:: ይህ ምን ማለት ነው? ብዙ ሰዎች የዶክተሩን አባባል የአቶ መለስ መጠቀሚያ ነበርኩ የሚል አንድምታ እንዳለው ይገልጻሉ:: በእኔ እምነት ይህ የዋህነት ነው:: ከአቶ መለስ ባልተናነሰ ሁኔታ አቶ ስዬ የህወሓት አድራጊ ፈጣሪ እንደነበሩ መዘንጋት የለብንም:: እናም በዚህ ሴራ (ነጋሶን መጠቀሚያ በማድረጉ ሂደት) ውስጥ

አቶ ስዬ የሉብትም ማለት ዘበት ነው፡፡ ዶ/ር ነጋሶ ለመጀመያ ጊዜ ይቅርታ የጠየቁት በ1999 ዓ.ም በአሜሪካ ሚኒሶታ ከተማ ከኦሮሞ ተወላጆች ጋር ባካሄዱት ስብሰባ ላይ ነበር፡፡ እንግዲህ ባለፈው ሐሙስ በግዮን ሆቴል የጠየቁት ይቅርታ በድጋሚ መሆኑ ነው፡፡ አቶ ገብሩ አስራት በበኩላቸው በ1997 ዓ.ም የካቲት ወር ተቃዋሚዎች በመስቀል አደባባይ በጠሩት ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ተገኝተው በተለይ ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ጋር በተያያዘ የተሰራው ስህተት «እኔም ስለነበርኩበት ከተጠያቂነት አልድንም» በማለት የኢትዮጵያን ህዝብ ይቅርታ ጠይቀዋል፡፡ አቶ ስዬ ግን አሁንም እምቢተኛ ናቸው፡፡

በ2000 ዓ.ም የመጀመሪያ ወራት አቶ ስዬ ወደ አሜሪካ አቅንተው በዚያ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ባነጋገሩበት ወቅት ይቅርታ እንዲጠይቁ ከስብሰባው ተሳታፊዎች ሀሳብ ተሰንዝሮ ነበር፡፡ አቶ ስዬም «እዚህ አዳራሽ ውስጥ በተለያየ አጋጣሚ የኢህአፓ አባላት የነበራችሁ፣ ደርግ ውስጥ ያገለገላችሁ፣ መኢሶን የነበራችሁ ልትኖሩ ትችላላችሁ፡፡ ሁሉም በየፊናው ስህተት ሰርቷል ሁላችንም የይቅርታን ሂሳብ በማወራረድ ጊዜ ከምናጠፋ ወደፊት ምን ማድረግ እንዳለብን ብንወያይ ይሻላል» የሚል ምላሽ ነበር የሰጡት፡፡ ይህ አባባል አሳማኝ አልመሰለኝም፡፡ የራስን ጥፋት የደርግ አባላት ከሰሩት ጥፋት ጋር እያነፀፀሩ «እናንተ ካልጠየቃችሁ እኔ አልጠይቅም» ማለት ተገቢ አይደለም፡፡ ለ16 ዓመታት ያህል በትጥቅ ትግል ከተፋለሟቸው ሰዎች ጋር ራስን እያነፃጸሩ ይቅርታ አልጠይቅም ማለት፤ ብቻውን ይቅርታ ያስጠይቃል፡፡

ጉዳዩ የስዬ ይቅርታ የመጠየቅ/አለመጠየቅ ግለሰባዊ ጉዳይ ብቻ ሆኖ መታየት ያለበት አይመስለንም፡፡ የኢትዮጵያን ህዝብ አመኔታ ለማግኘት ከተፈለገ ያለው ምርጫ ይኸው ብቻ ስለሆነ ነው፡፡ አለበለዚያ ግን «ቂም ይዞ ጸሎት» ይሆናል፡፡ ይቅርታ የመጠየቅ ክቡር ስብዕና የተመካው ለህዝብ ከሚኖረው አክብሮትና እንዲፈጠር ከሚፈለገው የመቻቻል ስርአት አንፃር እንጂ በተለያየ ተሳትፎ ውስጥ ያለፉ ሌሎች ወገኖች ለጉዳዩ በሚያሳዩት ምላሽ የሚሆንበት ምንም ስነ-አመክንዮ የለም፡፡ በተለይ በግለሰብ ነፃነት ላይ የተመሰረተ መርህና ፍልስፍና በሚያራምድ ፓርቲ ውስጥ የሚቀላቀል ማንኛውም ግለሰብ ለመርሆቹ ታማኝ ከሆነ የተገደበ ማንነት የሌላቸው «ሌሎች» አካላት ይቅርታ አለመጠየቃቸው፤ ከደሙ ንፁህ የመሆንን ዋስትናም አያጎናጽፍም፡፡

ሰሞኑን ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም በተቃውሞ ጎራ ተሰልፈን በቆየንባቸው ዓመታት የመረጠንን ህዝብ ለማገልገል ብቁ ሆነን አልተገኘንም በማለት «ህዝብ ይቅርታ ሊጠየቅ እንደሚገባ» በይፋ ተናግረዋል፡፡ ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራውም በተመሳሳይ ሁኔታ ፓርቲያቸው አንደኛ አመቱን ሲያከብር በቀድሞ ቅንጅት አመራሮች መካከል ክፍፍል በመፈጠሩና ሕዝቡን በማሳዘናችን ይቅርታ እንጠይቃለን ብለዋል፡፡ እንግዲህ በተቃውሞ ጎራ የተሰለፉ ወገኖች የሚጠበቅብንን ያህል አልሰራንም ብለው ይቅርታ እየጠየቁ ባሉበት

ሁኔታ የገኘው ፓርቲ ከፍተኛ የአመራር አባል የነበረ ሰው ድሮም አሁንም ትክክል ነኝ ብሎ ገዢውን ፓርቲ «ለመፋለም» ተቃዋሚዎችን ሲቀላቀል አንድም የተቃውሞ ጎራውን ከልቡ አላመነበትም:: አሊያም ደግሞ ራስን በሰማየ ሰማያት ላይ ከማስቀመጥ ግለሰባዊ ጀብደኝነት ባህሪ የሚመነጭ ነው::

አንድነት ፓርቲም ቢሆን ህዝብን የሚያከብር ከሆነ እንዲህ አይነቱን ውዥንብር አጥርቶ መሄድ ያለበት ይመስለኛል:: ፕሬስ የህግ የበላይነት እንዲሰፍን፣ ተጠያቂነት እንዲኖር በስልጣን ላይ ያሉ ወገኖች የሚያራምዱት ኢ-ዴሞክራሲያዊ አሰራር እንደሚኮንን ሁሉ፣ ተቃዋሚዎች ውስጥም ችግር ሲኖር ፕሬሱ ችግሩን ማጋለጥ አለበት:: በግሌ አንድነት ውስጥ አንድ መሰረታዊ ችግር ይታየኛል:: የግሉ ፕሬስ ገዢውን ፓርቲ ብቻ እንዲኮንን እንዲያጋልጥ በተቃዋሚዎች በኩል ያለውን ድክመት ግን ፕሬሱ አይቶ እንዳላየ አድበስብሶት የማለፍ ግዴታ እንዳለበት አድርጎ የመገንዘብ ችግር ነው:: ተቃዋሚዎች ለዚህ የሚሰጡት ምክንያት «ህዝብ ተስፋ ይቆርጣል» የሚል ነው:: ይህ አይነቱ ድምዳሜ ደግሞ እጅግ የተሳሳተ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ ነገር ብቻ መስማት እንደሚፈልግ አድርጎ አሳንሶ የመመልከት ቂልነት ነው:: በመሰረቱ ከፓርቲዎቹ ይልቅ ፕሬሱ ለህዝብ ቅርብ ነው:: የህዝብን እሮሮ በቅርብ ለማድመጥም እድል አለው:: ህዝብ የማይፈልገው ነገር ቢጻፍ እንኳን በተለያየ መንገድ ከፓርቲዎቹ ቀድሞ ሀሳቡን ለፕሬስ ተቋሙ የመድረስ እድል አለው:: «የውስጥ ችግራችንን ማንም አይስማው»፣ የአደባባይ መነጋገሪያ የሆኑ ጉዳዮችን ሳይቀር «ለምን አልሸፋፈናችሁም፣ የፕሮፌሰር እከሌ መጣጥፍ ለምን አተማችሁ?» ብሎ ማሳቀቅ የሌላ ሳይሆን የኢህአዴግ ወራሽ መሆን ነው::

ከዚህ አንጻር አቶ ስዬ ከባህሪያቸው ጋር የሚጣጣም ፓርቲ ያገኙ ይመስለኛል:: በጥር ወር 2000 ዓ.ም ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም የአቶ ስዬን ቃለምልልስ መነሻ በማድረግ አዲስ ነገር ጋዜጣ ላይ በጻፉት መጣጥፍ «ስዬ ተለውጧል» ብለው ነበር:: በበኩሌ በፕ/ር መስፍን ሐሳብ አልስማማም:: አቶ ስዬ አልተለወጡም:: አሁንም አምባገነን ናቸው:: በሚያዚያ እና ግንቦት 2000 ዓ.ም ከአውራምባ ታይምስ ጋር ሁለት ጊዜ ሰፋፊ ቃለምልልስ ማካሄዳቸውን አንባቢያን አይዘነጉትም:: በወቅቱ የአንባቢ አስተያየት ምን እንደሚመስል እየደወሉ በቅርብ ይከታተሉ ነበር:: ነገር ግን የተስፋዬ ገ/አብ «የጋዜጠኛው ማስታወሻ» መጽሀፍ የካቲት 10/2001 ዓ.ም በአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ዳሰሳው ሲሰራ አቶ ስዬን በተመለከተ ደራሲው ያሰፈረውን ጽሁፍ በጋዜጣው ላይ በከፊል መጠቀሱ አቶ ስዬን ክፉኛ አበሳጭቷል:: አጋጣሚ ሆኖ ደራሲው አቶ ስዬን በመጽሀፉ ውስጥ በመልካም ሁኔታ አልጠቀሳቸውምና አውራምባ ታይምስ ምን ማድረግ እንደነበረበት ባይገባኝም፣ ጋዜጣው የእርሳቸውን «መልካም ገጽታ» ብቻ የመጻፍ ግዴታ የተጣለበት ይመስል መበሳጨታቸው እጅግ አስገርሞኛል::

አቶ ስዬ ለረጅም ዓመታት ካካበቱት «ነገሮችን በጉልበት የመፍታት ልምድ» አንጻር ለሰላማዊ ትግል አዲስ ስለሆኑ ለእርሳቸው የሚቀርብ የትግል ስልት ከሚከተሉ ተቃዋሚ ወገኖች ይልቅ «በሰላማዊ ትግል ቆርበናል» ከሚሉት ጋር መቀላቀላቸው ትግሉን ፈታኝ ሊያደርግባቸው ይችላል:: በተለይ ሀሳብን በነፃ የመግለጽ መብትን የማክበር ትዕግስት ከሌላቸው ሳይውሉ ሳያድሩ የትግል ስልት መቀየር ሳይሻላቸው አይቀርም::

# የአንድነት የ'አንገት ሹራብ'
# ዋጋው ስንት ነው?

*በወሰንሰገድ ገ/ኪዳን*

«....እኔና አንተ አንድ ነበርን
ትናንት በደጉ ዘመን
አሁን በከፋው ሰዓት
ምንም አይደለን
ደግሞም ምንም አይደል
የትናንት አንድነታችን
አንድ ነን እንላለን እንጂ
ልማድ ሆኖበት አፋችን
ብዙ ነው ልዩነታችን....»

በዚህ ጽሁፍ እንደመንደርደሪያ የቀነጨብኳት ይህቺ ግጥም ርዕሷ «እኔና አንተ» የሚል ነው:: የዛሬ አራት አመት ግድም (1999 ዓ.ም መግቢያ አካባቢ) የከተብኳት ናት:: ከቀድሞው የቅንጅት አውራዎቹ አመራሮች ጋር ክስ ተመስርቶብኝ ቃሊቲ እስር ቤት ተወርውሬ ነበር:: በዚህ የእስር ቤት መራር ኑሮ ውስጥ በርካታ «መራር እውነቶች»ን አጣጥም ዘንድ ተገድጃለሁ:: እነዚያን መራር ዕውነቶች በስድም፣ በግጥምም ከትቦ የማኖር ልማድ ነበረኝ:: በትዝታም፣ በታሪክም መዘክርነት ጭምር::

እነሆ ከአራት ዓመት በኋላ «እኔና አንተ» ስል የፃፍኳት ግጥም ትዝታ ተቀሰቀሰብኝ፡፡ ከእነ መራር ዕውነቷ፡፡ ትዝታዬን የቀሰቀሰችብኝ ህዳር 17 ቀን 2002 ዓ.ም የሰማሁት «የአንድነት» ፓርቲ ዜና ነው፡፡

ዜናው የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት የነበሩት የተከበሩ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ እና በሽግግር መንግስቱ ወቅት መከላከያ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ስዬ አብርሃ አንድነት ፓርቲን መቀላቀላቸውን የሚያበስር ነው፡፡

የእነዚህ ታዋቂ ሰዎች አንድነት ፓርቲን መቀላቀል ብዙም አላስደነቀኝም፡፡ በተናጠል ከመታገል ይልቅ በጋራ መታገል ወደ ውጤት ሊያመራ ይችላልና፡፡ በዚህ ጥሬ ዕውነት ላይ አንዳችም ጥርጣሬ የለኝም፡፡

የሆኖ ሆኖ የእነ ዶ/ር ነጋሶ አንድነትን የመቀላቀል በተመለከተ ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው «የሁለቱ ሰዎች መቀላቀል ፓርቲውንም ትግሉንም ያጠናክረዋል» ሲሉ መናገራቸውን በሰማሁ ጊዜ በዓይነ ህሊናዬ አራት ዓመታት ያህል የኋሊት እንድጓዝ ተገደድኩ፡፡ እናም ብዙ፤ እጅግ ብዙ ነገር ታወሰኝ፡፡

የቀድሞው የቅንጅት አመራሮች እስር ቤት መግባት ታወሰኝ፡፡ ከእስር መውጣታቸውም ታወሰኝ፡፡ የአንድነት ፓርቲ ምስረታ ሂደት ታወሰኝ፡፡ የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ዳግመኛ መታሰር ታወሰኝ፡፡ የእነ ፕሮፌሰር መስፍን በሀሳብ መለየትና ከፓርቲው መታገድ ታወሰኝ፡፡ የዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም ከአንድነት ፓርቲ አመራርነት መልቀቅ ታወሰኝ፡፡ ምን ያልታወሰኝ ነገር አለ?

ከእነዚህ ሁሉ ትውስታዎቼ መሀል የዶ/ር ያዕቆብ «ፖለቲካ በቃኝ» ማለት እና ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው የእነ ዶ/ር ነጋሶ አንድነት ፓርቲን መቀላቀል ትግሉን ያጠናክራል ሲሉ ያደረጉት ንግግር «ገዘፈብኝ»፡፡ እናም መጠናከር ማለት ምንድነው? የጥንካሬ መለኪያውስ? ስል ራሴን ጠየቅሁኝ፡፡

ይህ ጥያቄዬ ያንን መራር እውነታ አስታውስ ዘንድ ግድ አለኝ፡፡ የአንድነት ሹራቡን ትውስታ፡፡ ለዚህ ነው የዚህን ጽሁፍ ርዕስ «የአንድነት አንገት ሹራብ ዋጋው ስንት ነው?» ለማለት የደፈርኩት፡፡ ይህም ከድፍረት ከተቆጠረ፡፡

## መራሩ ዕውነት

መራሩ ዕውነት የተከሰተው ከአራት ዓመት በፊት ነው፡፡ በ1999 ዓ.ም መግቢያ አካባቢ፡፡ ያኔ የቀድሞው የቅንጅት አመራሮች እና ጋዜጠኞች እስር ቤት ነበሩ፡፡- ነበርን፡፡

ያኔ የኢትዮጵያ ህዝብ የቅንጅት ታሳሪዎች በይቅርታ መፍታት እንዲህ እውን ሊሆን ቀርቶ ምን እየተደረገ እንዳለ በጭምጭምታ እንኳ የሰማው ነገር አልነበረም፡፡ የአገር ሽማግሌዎች አደራዳሪነት እንኳንስ ለህዝብ ለታሳሪዎቹ ቤተሰቦች ምስጢር ነበር፡፡

ይሁን እንጂ እስር ቤት ውስጥ የተለየ ሁኔታ ነበር፡፡ የድርድሩን ሀሳብ በመቀበልና ባለመቀበል ጉዳይ ላይ በታሳሪዎቹ የቅንጅት አመራሮች መሀል ሰፊ የአመለካከት ልዩነት የተከሰተበት ወቅት ነበር፡፡ የሀሳብ ልዩነትን ከማቻቻል ይልቅ ወደመነቋቆር እና ወደግልጽ ፀብ የተደረሰበት ወቅት ነበር፡፡

ይህንና ይህን መሰሉ ቁርቋሶ ግን እዚያው በታሳሪዎቹ መሀል የሚቀር እንጂ ወደሌላ አካል ወይ ወደቤተሰብ ይሸጋገራል የሚል እምነትም ግምትም የነበረው አለ ማለት የሚያስችል ሁኔታ አልነበረም፡፡ ያን ጊዜ የሆነው ግን የዚህ ተቃራኒ ነው፡፡

የታሳሪዎች ቤተሰብም ሆነ ሌላ እስረኞቹ የፖለቲካ ሰለባ መሆናቸውን እንጂ እርስ በርሳቸው የአመለካከት ልዩነት ሰለባ መሆናቸውን አያውቁም፡፡ የሚያውቁበትም መንገድ  አልነበረም፡፡ የሁሉም ቤተሰብ ሁሉንም እስረኛ በአንድ አይን የሚመለከትበት የአቅሙንና ታሳሪውን ያበረታታል የሚሉትን ስጦታ የቤተሰቡ አባል ከሆነው ሰው ውጪ በመስጠት አክብሮቱን የሚገልጽበት ወቅት ነበር፡፡

በዚህ ጊዜ ነበር የኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው ቤተሰብ አባል የሆነ አንድ ሰው ለዶ/ር ያዕቆብ የአንገት ሹራብ በስጦታ መልክ ይዞ መጣ እና ስጦታውን ለዶ/ር ያዕቆብ በአክብሮት  ሰጠ፡፡ ያኔ በመጠየቂያ ቦታ ላይ ሁላችንም ቆመን ነበር፡፡

«ምንድነው?» አሉ ኢንጅነር ግዛቸው

«ስጦታ»

«ተቀበለው!»

እስር ቤት ውስጥ በኢ/ር ግዛቸውና በዶ/ር ያዕቆብ መሀከል የተከሰተውን የአመለካከት ልዩነት ያላወቀው የዋሁ ስጦታ ሰጪ ሰው ግር እያለው ከዶ/ር ያዕቆብ ዕጅ ስጦታውን መልሶ ተቀበለ፡፡

«ለዶ/ር እከሌ ስጠው!»

ስጦታ አቅራቢው ግር እያለው ስጦታውን አሳልፎ ለሌላው ሰው ሰጠ፡፡ ከኢ/ር ግዛቸው ጋር በድርድሩ ጉዳይ አንድ አይነት አመለካከት የነበረው እስረኛ በዚህ መልክ ያላሰበውን ስጦታ አገኘ፡፡ የአንገት ሹራብ፡፡

በዚህ የአንገት ሹራብ ስጦታ የተነሳ የተከሰተው ክስተት ተራና እዚህ ግባ ሊባል የማይችል ይሆን ይሆናል፡፡ ለእኔና ለእኔ መሰል በፖለቲካ ሰበብ ለእሥር ለተዳረጉት ሰዎች ግን እያመመንም ቢሆን መራሩን እውነት እንድንጎነጭ ያደረገ አጋጣሚ ነበር፡፡ ድርጊቱ አሸማቃቂ ነው፡፡ አሳፋሪ ነው፡፡ ተስፋ የሚያስቆርጥ ነው፡፡ የዓላማ ምንነትን የሚያጠያይቅ ነው፡፡ ለአንድ ዓላማ በአንድ የመቆምን ትርጉም የሚያዛባ ነው፡፡ እምነትን የሚያነጋ ነው፡፡በወቅቱ እነዚህ ናቸው ወይ የኢትዮጵያን ህዝብ መምራት እንችላለን ሲሉ የኖሩት? የሚል ጥያቄ እንዲነሳ ያስገደደ ድርጊት ነው፡፡ ለዚህ ነው ለመንደርደሪያነት የተጠቀምኩበትን ግጥም አንገቴን ደፍቼ ለመፃፍ የበቃሁት፡፡ እንዲህ ብዬ የቀጠልኩት፡-

«...ዘንድሮ

እንኳንስ እኔና አንተ

ሁለት ነጠላ ሰዎች

በአፍታም ተግባብተው አያውቁ

የየራሳችን መንፈሶች

አንደኛው እኔ መንፈስ

አንደኛው እኔን ሲስበው

እውነት እየመሰለው

እኔና አንተን አመሳጥረው

እኔና አንተን አሸናግለው

አንድ ነን ያሉት ውሸት ነው

አንድነን ያሉት ሐሰት ነው

አንደኛው እኔ መንፈሴ

ከሌላው የተጣበቀው

ሀቅ አይገለጥ መስሎት ነው....»

አዎ! የአንገት ሹራቡ (ስከርቭ) ስጦታ እንዳጣጥም ያደረገኝ መራር ዕውነት እንተዋወቅ ነበር ወይ? የሚለውን ነው:: የቀድሞው የቅንጅት አመራሮች (እስር ቤት የገቡት) ይተዋወቁ ነበር ወይ? ዴሞክራሲ የሚባለውን ነገር በእርግጥ ያውቁት ነበር ወይ? የፖለቲካ ትግል የሚጠይቀውን ብርታትና ስብዕናስ ነበራቸው ወይ? ወዘተ ወዘተርፈ....

ለእኔ መልሱ እንዲያው ዝም ነው:: ዝም እና ዝም ብቻ:: ምነው ቢሉ ከእስር ቤት በኋላ ከአንድነት ፓርቲ ምስረታ እስካሁን ድረስ ያየሁት ያንኑ የሚጎፈንን መራር እውነት ነው:: ያንኑ ራሱን የደገመ የአመለካከት ንቅዘት::

## ንቅዘቱ ሲደገም

ለአንድነት ፓርቲ ምስረታ ጉልህ ሚና ከተወጡት መሀል በግንባር ቀደምነት የሚጠቀሱት ከእስር የተፈቱት የቀደሞው የቅንጅት አመራሮች መሆናቸው እውነት ነው:: ከእስር መፈታት በኋላ የሆነው ነገር ሁሉ ሆኖ የወጣውም ወጥቶ የተራገፈውም ተራግፎ በሰላማዊ የትግል መሠረት ላይ የቆመው አንድነት በትግሉ ላይ ተስፋ የቆረጠውን ህዝብ በጥቂቱም ቢሆን ተስፈኛ ማድረግ ችሎ ነበር::

ይኼ ነበር ነው:: ነበር ብቻ::

ነገር ግን በጥቂቱም ቢሆን ጭል ጭል ያለው የትግልና ተስፋ ባልታጠቀ መንገድ ለመምሸክሸክ በቃ:: በእነ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም መባረር::

ለእነ ፕ/ር መስፍን ከፓርቲው መታገድ (መባረር) እንደምክንያት የተጠቀሰው (እኔ እስከገባኝ ድረስ) በፓርቲው አካሄድ ላይ የአመለካከት ልዩነት እንዳላቸው የሚገልጽ ጽሁፍ በማሰራጨታቸውና አባላቶችን ለማወያየት መሞከራቸው ነው::

ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ስኬት፣ ውበትና ጌጥ የአመለካከት ልዩነትን ማንፀባረቅ መቻል በተንፀባረቀው ሀሳብ ላይ መሚገት፣ መወያየትና ለአሸናፊው ሀሳብ ተገዝቶ አብሮ መጓዝ መቻል ማለት ነው:: እንጂ የአመለካከት ልዩነትን ማንፀባረቅ እንደሥርዓት አልበኝነት ተቆጥሮ ለእገዳ የሚያበቃ አይደለም:: አልነበረምም::

ይህ ሁኔታ የሚያሳው 'ከእኔ ሀሳብ የተለየ የተረገመ ነው፣ እኔ ያመንኩትን ያላመነ ሊሳደድ የሚገባው ነው' የሚለውን ያረጀ ያፈጀ ባህል መኖሩን ነው:: ልክ ዶ/ር ያዕቆብ እስር ቤት ውስጥ እንደተቀማው የአንገት ሹራብ (ስከርቭ) የዴሞክራሲን ስጦታ መቀማት ነው:: ራስን አለማወቅና አለመተዋወቅ ጭምርም ነው:: ስለዴሞክራሲ ምንነት ጠልቆ አለማወቅም ነው::

## የአንገት ጌጡ

አንድነት ከተመሰረተ በኋላ በጉዞው ውስጥ በውጪያዊ ኃይል ምክንያት የተነሳ መሪውን ብርቱካን ሚደቅሳን አጣ:: በፓርቲው ውስጥ በተነሳ የሀሳብ ልዩነት ምክንያት አንቱ ከተባሉት የፖለቲካ ታጋዮች መሀል ፕ/ር መሥፍንን በራሱ እጅ አጣ:: አውራ ከሚባሉት መሀል ዶ/ር ያዕቆብ ፓርቲውን ለቀው ወጡ::

ከዚህ በኋላ ነበር ፓርቲው ምን ቀረው? ብዬ ራሴን የጠየቅኩት:: ለጥያቄዬ መልስ ማግኘት አልቻልኩም ነበር:: እነ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ አንድነትን መቀላቀላቸውን በተመለከተ ማረጋገጫውን እስከሰማሁበት ጊዜ ድረስ::

ለካስ ከብርቱካን መታሰር፣ ከነፕሮፌሰር መስፍን መታገድ፣ ከዶ/ር የዕቆብ መልቀቅ በኋላ ፓርቲው የቀረው «የአንገት ጌጥ» ብቻ ነበር:: ለራሴ ጥያቄ ራሴ ያገኘሁት መልስ ራሱን የቻለ ምፀት ነው ልትሉ ትችላላችሁ:: የእነ ዶ/ር ነጋሶ አንድነትን መቀላቀል ለእኔም ራሱን የቻለ ምፀት ነው የሆነብኝ:: ምነው ቢሉ የአንገት ሹራብ ለእኔ ከልብስነቱ ይልቅ ጌጥነቱ ነውና ጎልቶ የታየኝ::

በእርግጥም የአንገት ሹራብ (ስከርቭ) አፈጣጠሩ ለጌጥ ነበር:: በፈረንሳዊው ንጉስ ሉዊ 15ኛ ዘመን:: የሉዊ 15ኛ ወታደሮች አንገታቸው ላይ እንደዘበት ሽብ አድርገው የታዩት ሹራብ እየዋለ እያደረ እየተሻሻለ እየተሻሻለ

መጥቶ ከረሻት ለመሆን እንደበቃ በአንድ ወቅት ማንበቤን አስታውሳሁ:: ያቺ አንገት ላይ ሸብ የተደረገች ጨርቅ «የቤተ-መንግስት መታያ» ለመሆን በቃች ማለት ነው::

ልክ እንደዚያው ሁሉ በሀሳብ ልዩነት ወሳኝ ታጋዮቹን ያጣውን አንድነት የእነ ዶ/ር ነጋሶ መቀላቀል ትግሉን ያጠናክራል ብሎ መናገር ከእነ ዶ/ር ያዕቆብና ፐ/ር መስፍን ላይ የትግልን የአንገት ሹራብ ነጥቆ በከረሻት እንደመቀየር ያለ ምፀት ይሆናል::

ዶ/ር ነጋሶ እና አቶ ስዬ ፓርቲውን ማጠናከር አይችሉም ለማለት አይደለም የፈለግኩት:: ሀሳብ አመንጭቶ በሀሳብ ተለያይቶ በሀሳብ የበላይነት መረታታት የማይችል አመራር የነገሰበት ፓርቲ ውስጥ ገብተው የሚያመጡት ውጤት አልታይ ቢለኝ እንጂ:: «የአንገት ጌጡ»ን ያስታወሰኝ::

ለዚህ ነው እነ ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ እና አቶ ስዬ ለአሁኑ አንድነት ጌጥ ናቸው ወይስ ለውጥ? በማለት ብዕሬን ለማንሳት የደፈርኩት:: ይህም ነው የአንድነት አንገት ሹራብ ዋጋው ስንት ነው? ያሰኘኝ::

# አፍሪካና የሙስና ደረጃ ሪፖርት

**በአለማየሁ ገ/ማርያም /ፕሮፌሰር/**

ዓለም አቀፉ የፀረ-ሙስና ጥምረት «ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል» /Transparency International – TI - «ቲ.አይ.»/ በቅርቡ፣ የ2009 የዓለም አገራት የሙስና ደረጃን (Corruption Perceptions Index – CPI - ሲ.ፒ.አይ.) ይፋ አድርጓል:: ዳግም ከእንደገና ከዓለም አሕጉራት መካከል አፍሪካ እጅግ ወሳኝ መንግስታት የሚገኙባት ሆና የመመረጥ ክብርን አግኝታለች:: የደረጃው ስንጠረዥ በኢትዮጵያ፣ በሱዳን፣ በዚምባቡዌ፣ በኢኳቶሪያል ጊኒና በኬንያ ባሉ የመንግሥት ሥርዓቶችና በሶማሊያ የጦር አበጋዞች በተቀዳሚነት የተያዘ ነው::

ሲ.ፒ.አይ.፣ በዓለም ዙሪያ በ180 አገራት እና ግዛቶች ያለን ሙስና የሚለካው እንደ አፍሪካ ልማት ባንክ፣ «ኢኮኖሚስት ኢንተሊጀንስ ዩኒት»፣ «አይ.ኤች.ኤስ ግሎባል ኢንሳይት»፣ «ኢኒስቲትዩት ፎር ማናጅመንት ዴቨሎፐመንት»፣ የአለም ባንክ እና «ዎርልድ ኢኮኖሚክ ፎረም» ያሉ ድርጅቶች በሚያቀርቡት መረጃና ትንታኔ ላይ በመመስረት ነው::

ሙስና «በአደራ የተሰጠን ሥልጣን ለግል ብልፅግና አላግባብ በመጠቀም» ማለት ነው ይላል «ቲ.አይ.» የሙስናን ትርጉም ሲያስቀምጥ:: በዚያ ትርጓሜ፣ የላይኞቹ የአፍሪካ አገራት የሙስና ደረጃ ውጤት አስደንጋጭ ነው - 3.0 ወይም ከዚያ በታች::

በተወሰኑ አገራት ያለው የሙስና አዝማሚያ ለመቀልበስ አዳጋች የሆነ ገጽታ ያለው ይመስላል:: ለምሳሌ፣ ኢትዮጵያ በ2002ቱ የደረጀ ሰንጠረዥ ያገኘችው ውጤት 3.5 ነበር:: ገዥው ሥርዓት በደማቅ ሥነ-ሥርዓት የፌዴራል የጸረ-ሙስና ኮሚሽንን ካቋቋመ ከስምንት ዓመታት በኋላና ሙስናን በመዋጋት «ከፍተኛ ስኬቶች» መመዝገባቸውን በየወቅቱ ካስታወቀ በኻላ፣ በ2009 ኢትዮጵያ ያገኘችው ውጤት አስደንጋጭ ነው - ወደ 2.7 ነው ያሽቆለቆለው::

የኢትዮጵያ የፌዴራል የጸረ-ሙስና ኮሚሽን አምኖበት የተቀበለ እንደሚመስለው፣ በአፍሪካ የተንሰራፋው ሙስና ከአሁን በኋላ እንደቀላል የወንጀል ጉዳይ፣ ጥቂት የመንግስት ባለሥለጣናትንና ሌሎችን በጉቦ፣ በዝርፊ፣ በማጭበርበርና በውንብድና መክሰስ ብቻ ተደርጎ መውሰድ የሚቻል አይደለም:: የ«ቲ.አይ.» መስራችና ሊቀመንበር ፒተር ኤይንግ እንደሚያስገነዝቡት፣ «ሙስና ቢያንስ በሶስት መንገዶች የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እንዲፈፀሙ መንገድ ይጠርጋል:: እነዚህም፣ መድሎን ቀጣይ ያደርጋል፣ ሙሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊና ባሕላዊ መብቶች እውን እንዲሆኑ እንቅፋት ይሆናል፣ የበርካታ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ጥሰቶች ምክንያት ይሆናል::» ከዚህም በላይ፣ ሙስና የሕግ የበላይነት አሰኳል እንዲቀጭጭና ዜጐች በፖለቲካ መሪዎች፣ በመንግስት ባለሥልጣናትና በፖለቲካ ተቋማት ላይ ያላቸውን አመኔታ የሚያጠፋ ነው::

በአፍሪካ፣ድሃውና ኃይል የሌለው ነው የሙስናን ቀንበር የሚሸከመው:: የፖለቲካ መሪዎችና የመንግስት ባለሥልጣናት ለወሳኝ የት/ቤት፣ ሆስፒል፣ መንገድና ለሌሎች ሥራዎች/የማሕበረሰብ ፕሮጀክቶች መዋል የሚገባቸውን ኃብቶች የራሳቸውን ኪስ ለማሳበጥ መጠቀማቸው ሲታይ፣ ሙስና በአጉሪቷ ድሃ ላይ ምን ያህል አስከፊ ጉዳት እንዳደረሰ መገንዘብ ይቻላል:: ለምሳሌ በተለያዩ መንገዶች ማለትም ሕዝባዊ የገንዘብ ድጎማን በግላጭ በመስረቀና በመመዝበር፣ መንግስታዊ ንብረቶችን አላግባብ ለራስ ጥቅም በማዋል፣ አላግባብ ክፍያዎችንና ጥቅሞችን ለማጋበስ መንግስታዊ ሥልጣንና ኃላፊነትን በመጠቀም በኢትዮጵያ የሚፈፀሙ የሙስና ወንጀሎች የተለመዱ ናቸው:: የአገሪቱ የሙስና ተግባሮች ለሂሲና አስደንጋጭ ናቸው:: የሕክምና መድሃኒቶችና ሌሎች አቅርቦቶች ለግል ጥቅም የሚውሉ በመሆናቸው በሕዝብ ሆስፒታሎች የሚሰሩ ዶክተሮች ታማሚዎቻቸውን ማከም አልተቻላቸውም:: ለሕዝቡ በእርዳታ መልክ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ መድሃኒቶችና የሕክምና አቅርቦቶች ታሪፍ ይጣልባቸዋል:: ነጋዴዎች እንደሚያቀርቡት አቤቱታ፣ ዳጐስ ያለ ጉቦ ካልከፈሉ ወይም ባለሥልጣኖችን እንደ አፍ ማስያዥያነት አጋራቸው አድርገው ካልተጠቀሙ በስተቀር የንግድ ፍቃድ ማግኘት ቸይቻላቸውም ያሰማሉ::

በሕገ-ወጥ ግበይቶችና ማጭበርበር የሕዝብ ንበረቶች በሥርዓቱ ደጋዎች ወይም ባለሥልጣናት ባለቤትነት ይያዛሉ:: ባንኮች ካለበቂ ወይም ትክክለኛ ማስያዣ በሚሊዩኖች የሚቆጠር ዶላር ለሥርዓቱ ደጋፊዎች ወይም ባለሥልጣናት ያበድራሉ:: ነጋዴዎች በመንግስታዊ ጫረታዎች ወይም የውል ሥምምነቶች ላይ ለመሳተፍ ወፍራም ጉቦ ወይም እጅ-መንሻ መክፈል ይጠበቅባቸዋል:: በአምጭነትና ላኪነት የሚሳተፉ ነጋዴዎች በጉሙሩክ ኃላፊዎች ገንዘብ እንድንሰጥ እንገደዳለን የሚል አቤቱታ ያሰማሉ:: በበርካታ ከፍተኛ ፖለቲካዊ የፍርድ ሂደቶች እንደታየው፣ በፖለቲካዊ ጣልቃ ገብነትና ውንብድና አጠቃላዩ የፍትሕ ሥርዓት በሙስና የተጥለቀለቀ ነው:: ለእረፍት በከተማ በመኪና የሚዘዋወሩ ኢትዮጵያውያን በትራፊክ ፖሊሶች ገንዘብ እንዲሰጡ እንደሚገደዱ ይናገራሉ:: ከሁለት ወራት በፊት የቀድሞው የኢትዮጵያ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ የተቀናጀ ፖለቲካዊ ሙስና ለፖተቲካዊ ጥቅም ተብሎ እንደተፈጽመ መግለጻቸው ከፍተኛ ማስረጃ ነው:: ባለፈው ሳምንት የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ኃላፊ ኢያን ኬሊ፣ «በወቅቱ ጠ/ሚኒስትር ፓርቲ ከአሜሪካ የተሰጠ የ850 ሚሊዩን የምግብና የጸረ-ድህነት እርዳታ እየተከፋፈለ ያለው በፖለቲካ ደጋፊነት ላይ በመመስረት ነው» የሚለውን ውንጀላ አሜሪካ እየመረመረችው መሆኑን ገልፀዋል::

ባለፉት ሁለት ዓመታት በኢትዮጵያ ከፍተኛ የሙስና ጉዳዩች በሚዲያ ተዘግበዋል:: እንደፌዴራል የጸረ-ሙስና ኮሚሽን፣ በአንድ የሙስና ጉዳይ «16 ሚሊዩን የአሜሪካ ዶላር» የሚያወጣ ጥፍጥፍ ወርቅ እንዲሁ ከባንክ እንደተዘረፈ አረጋግጧል:: «በአገሪቱ ብሔራዊ ባንክ ከፍተኛ ውንብድና የተፈፀመ ሲሆን ይህም ብዙ ኢትዮጵያውያንን እንዳስደነገጠና በዚህም ሞሳኞች የኢትዮጵያ ሕዝብ ንብረት የሆነ ንፁህ የወርቅ ጥፍጥፎችን በባለስትራ በመቀየር ዘርፈዋል፤ ... በዚህ አደገኛና አሳፋሪ የወንጀል ቅሌት የተወሰኑ የባንኩ ሰራተኞች፣ ማናጀሮችና ሌሎች የመንግስት ቅጥረኞች ተሳትፈዋል::» በማለት ነበር ኮሚሽኑ ስርቆሹን የገለጸው::

ከቻይናዎች ጋር በሚያያዝ የቴሌኮሙኒኬሽን ጉዳይ ደግሞ አንድ ከፍተኛ የመንግስት ባለሥልጣን ለራሱና ለሌሎች የሥርዓቱ ባለሥልጣናት ጉቦ ለመቀበል ሲሞክር በምስጢር በመቅረጸ ድምጽ ተቀድቷል:: ኮሚሽኑ «በርካታ ኢትዮጵያውያንን ያስደመመ ሌላ የሙስና ጉደይ በኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን» መፈጸሙን ባቀረበው በሪፖርት ገልጾ የነበረ ሲሆን ጉዳዩ «በጨረታ ለቴሌኮሙኒኬሽኑ የመሳሪያዎች አቅርቦት» ለማረግ ጋር የተያያዘ ነበር:: ከወንጀል ምርመራ በኋላ ኮሚሽኑ «በአጠቃላይ 200 ሚሊዩን የኢ.ዶ. የሚጠጋ ገንዘብ በሙስና ማጭበርበርና ምዝበራ መጥፋቱን አረጋግጧል::»

በርካታዎቹ የአፍሪካ መንግስታት፣ ዓለም አቀፍ ለጋሾችንና ዓለም አቀፍ አበዳሪ ተቋማትን በጸረ-ሙስና ስም የማወናበድ ጨዋታ ለመጫወት ሞክረዋል:: ከኢትዮጵያ

የበለጠ ለዚህ ማስረጃ የትም የለም። ሥርዓቱ ኮሚሽኑን በ2001 ያቋቋመው ሙስናን ለማጥፋትና ስለሙስና ለማስተማር በሚል ዓላማ ነበር። ኮሚሽኑ፣ ከ2005 አንስቶ ከ15 ሚሊዬን በላይ ለሚሆኑ ሰዎች የሥነ-ምግባርና የጸረ-ሙስና ትምህርት እንዲሰጠና ሙስናን እንዴት መዋጋት እንዳለባቸው ለ267 የሥነ-ምግባር ኦፊሰሮች የማማከር አገልግሎት መስጠቱን ይናገራል። የአቃቤ ሕግ ዲፓርትመንት «ተፈጽመዋል በተባሉ 79 የሙስና ጉዳዮች የወንጀል ክስ መስርቷል፣ በ28ቱ የጥፋተኝነት ውሳኔን አግኝቷል።»

በ2007/08፣ ኮሚሽኑ ሙስናን በመከላከል ስትራቴጂ 325 ግለሰቦችን አሰልጥኗል፤ የ34 የመንግስት ቢሮዎችንና የንግድ ድርጅቶችንና 110 የፕሮኩርመንት፣ የፍቃድ፣ የፋይናንስ፣ የሰው ኃይል፣ የጤና፣ የትምህረት፣ የሚዲያና የሌሎች ተቋማት «ትግበራዎችንና የአሰራር ሥነ-ሥርዓቶችን ማሻሻያ አድርጎባቸዋል። «ያልተገባ ጥቅም በማግኘት/በመንግስት ላይ በደረሰ ኪሳራ ኮሚሽኑ 296 ተጠርጣሪዎችን መርምሯል፤ ተጠርጣሪዎቹ ለራሳቸው ብልጽግና በመንግስት ላይ አድርሰዋል የተባለው የገንዘብ መጠን 2180311361 የሚገመት መሆኑ እጅግ የሚያስደምም ነው። ከ296ቱ አብላጫዎቹ (34%) ሥልጣን አላግባብ በመጠቀም ምርመራ የተካሄደባቸው ናቸው። በሃሰተኛ ሰነድ /ማጭበርበር (30%)፣ በብልሹ አሰራር/አመኔታ በማጣት (13%)፣ በምዝበራ (8%)፣ ጉቦ በመቀበል (2%)ና ሌሎች (4%)። እንደ ኮሚሽኑ፣ «ፍ/ቤት የሙስና ወንጀል ለመፈጸም ዝግጅት ተደርጎባቸዋል በተባሉ 79ኝ ጌዳዮችን በተመለከተ ውሳኔውን አስተላልፏል።» በ66ቱ ጉዳዮች ላይ የጥፋተኝነት ወሳኔ ሰጥቷል። ከእነዚህ ውስጥ 31 የሚሆኑት ለኮሚሽኑ የተላለፉለት ናቸው። በባጀት ዓመቱ በ48 ክሶች ላይ ፍርድ ተሰጥቷል፤ ከእነዚህም ውስጥ 43ቱ ጥፋተኞች መሆናቸው ተረጋግጧል። የጥፋተኝነት ውሳኔ የተላለፈባቸው አብዛኛዎቹ ተከሳሾች ከአነስተኛ የገንዘብ ቅጣት ጋር የአጭር ጊዜ እስር ተላልፎባቸዋል።

በኢትዮጵያ ያለው ጠቅላላው የሥርዓቱ «የጸረ-ሙስና» ድራማ፣ ዓለም አቀፍ ለጋሾችና አበዳሪ ተቋማትን የማታለያ የፖለቲካ ቲያትር ነው። ከማለባበስ የዘለለ ፋይዳ የላቸውም። ከአገዛዙ ጋር በመልካም ቁርኝት ያለው አንድም ከፍተኛ ባለሥልጣን በሙስና አንዴም ተከሶ ወይም የወንጀል ምርመራ ተደርጎበት አያውቅም። ወንጀሎቹ ከዚህ ቀደም ተፈጽመው የማያውቁ፣ እጅግ ከፍተኛና አደገኛ ተፈጥሮ ቢኖራቸውም ስለምን የሞሳኞቹ የፍርድ እንደዘገየ ምክንያት አልሰጠበም። በአጠቃላይ የሥርዓቱ ግብ በሙስና ጉዳይ የበታች ባለሥልጣናትንና ሌሎችን በመክሰስ ትኩረትን ከራሱ ማስወገድ ነው።

አንድ ሰው በሚያስገርም መልኩ መለስተኛ «የማጣመም የምህንድስና ጥበብ» በኮሚሽኑ ሪፖርቶች ላይ በማድረግ የየሴክተሩን የሙስና ችግሮች በዝርዝር ከነትክክለኛ ው መጠኑና ስፋቱ ሊያብጠረጥረው ይቸርላል፤ እንዲሁም የበርካታዎቹን መንግስታዊ

ኤጀንሲዎች አጠቃላይ የብቃት ማነስ መግለጽ:: መረጃዎች እንደሚያሳዩትና ብዙም ማለት የማያሻው ምንድን ነው ዛሬ ከፍተኛ የሙስና ተግባሮች የሚያጋጥሙት «ሥልጣንን አላግባብ በመጠቀም» ሲሆን ይህም የሚጠቁመው የሕግ የላይነት አለመኖርንና ግለሰባዊና ተቋማዊ ተጠያቂነትንና ግልጽነትን የሚያሰፍኑ ሥነ-ሥርዓቶች፣ ሕጐችና ቁጥጥሮች በመሰረታዊ ደረጃ የሌሉ መሆናቸውን ነው::

በኢትዮጵያና በሌሎች የአፍሪካ ሥፍራዎች ሙስና መቋጫ የታጣለት ምክንያት ሥልጣንን የሙጡኝ የሚሉ ሰዎች ከሙስና በእጅጉ የሚጠቀሙ በመሆናቸው ነው:: በኢትዮጵያ የሙስና አ'ክቴክቶችና ተጠቃሚዎችን ኮሚሽኑ እንዲመረምር ማድረግ ግራ የተጋባና ውጤት የማያመጣ ነው:: ኮማሽኑ በጥብቅ የሙስና ምንጠራና ክስ በሚሊዮኖች የሚገመት የመንግስት/ሕዝብ ከጥፋት ማዳኑን ወይም መቀነሱን ይናገራል:: ይህ ጣዕም የሌለው የሚያስቅ ወሬ ነው:: ለአብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን ሙስና የሚያስቅ ጉዳይ አይደለም፣ ሆኖም ወንጀሉን በተመለከተ ጉልበት የለሽ ስሜት ይሰማቸዋል:: አጠቃላዩን የፀረ-ሙስና ጥረት የሚመለከቱት እጅግ ተዳክመውና ተስፋ ቆርጠው ነው:: ከሁሉም በላቀ በኢትዮጵያ ውስጥ ዛሬ የሙስና ቁጥጥር ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፤ ከአመራሩ አናት አንስቶ የሙስና ምርመራ ሊጀመር ይችላል? ቢሮክራሲያዊውን መመርመርና መክሰስ ይቻላል? ወይስ ለድራማዊ መስህብነት ሲባል በጥቂት ተሿሚዎችና የትራፊክ ፖሊሶች ላይ ትኩረት ማድረግ?

ጥርስ የሌለው የጸረ-ሙስና ኮሚሽን በማቋቋም ዓለም አቀፍ ለጋሾችን ለማስደሰት የሙስናን ችግር በወሬ ብቻ መፍትሄ ማበጀት አይቻልም:: በኢትዮጵያና በበርካታ የአፍሪካ አገራት ሙስና የመንግስት ዋነኛ ስራ ነው:: ውጤታማ የጸረ-ሙስና ጥረቶች በሕግ የበላይነት ላይ የተመሰረተ፣ ጠንካራ የዴሞክራሲ ባሕል፣ እና በእለታዊ ሕይወት ችግሩን መፋለም የሚያስችል ንቁ የዜጐች ተሳትፎን ይጠይቃል:: በአፍሪካ በጣም ዝቅተኛ ሙስና ይፈፀምባታል ተብላ በምትወሰደው ቦትስዋና፣ ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡ መንገደኞች ያልተለመደ መልዕክት የሚያስተላልፍ ትልቅ የእንኳን መጣችሁ ፖስተር በጋቦሮኒ አየር ማረፊያ ቆሟል:: እንዲህ ይላል ፖስተሩ :-«Botswana has ZERO Tolerance for Corruption. It is Illegal to Offer or Ask for a Bribe»

የፌዴራል የጸረ-ሙስና ኮሚሽን እንደሚለው በኢትዮጵያ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሙስና ምንጮች «ደካማ አስተዳደር፣ የማግልጽነትና ተጠያቂነት መታጣት፣ ዝቅተኛ የዴሞክራሲ ባሕልና ተለምዶ፣ አስከፊ ድህነትና የርትዕ መታጣት፣ የጐጂ ባሕሎች ትግበራዎች እና የሥልጣን ማዕከላዊነት፣ የዜጐች ተሳትፎ አነስተኛነት፣ የግልጽ ቁጥሮችና የግዴታ አሰጣጥ እጥረትና ዝቅተኛ የተቋማት ቁጥጥር» ናቸው:: እነዚህ ብቻ አይደሉም፤ የጠንካራ አስተዳደር፣ ተጠያቂነትና ግልጽነትና የሕግ የበላይነት አለመኖራቸው የአስከፊ ድህነት፣ ርትዕ መታጣት ... የስር መንስዔዎች ናቸው::

(አለማየሁ ገ/ማርያም በ«ካሊፎርኒያ ስቴት ዩኒቨርስቲ፣ ሰን በርናርዲኖ የፖለቲካ ሳይንስ  ፕሮፌሰር» ናቸው፡፡)

## የህግ የበላይነት

# ውስጣዊ ዲሞክራሲ የተሳናቸው ፓርቲዎች

**በግዛው ለገሰ**

በሀገራችን የሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች የህዝብን ውክልና ለመቀበል፣ ተቀብለውም የህዝቡን ጥቅም ለማስጠበቅ ብቁ ስለመሆናቸው የምንሰጋ ብዙዎች ነን፡፡ በርግጥም በውስጣቸው ያለው የእርስበርስ ሽኩቻ፣ የተልፈሰፈሰ አቋም፣ የጥቂት ሰዎች የበላይነት፣ እንዲሁም የፖለቲካ ግንዛቤ ማነስ የስጋቱ ምንጮች ናቸው፡፡ ለአጠቃላይ ህዝቡ የተሻለ አማራጭ ይቀርብለት ዘንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች መጠናከር ሚናው ከፍተኛ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ ዋናው መፍትሔ በውስጣዊ አደረጃጀታቸው ላይ ይበልጥ እንደሚመረኮዝ ይታመናል፡፡

በኢንስቲትዩት ኦፍ ሶሻል ስተዲስ፣ ዘ ሔግ የፖለቲካ ፕሮፌሰር የሆኑት ሞሐመድ ሳሊህ፣ «ዲሞክራሲያዊ ፉክክር ስለሚታይበት ምርጫ፣ ሥልጣን ስለመያዝ፣ እንዲሁም የመንግስትን ቦታ ስለመቆጣጠር መናገር ለፖለቲካ ፓርቲዎች ቀላል ነው፡፡ ይበልጥ ከባዱ ጥያቄ ግን ፖለቲካ ፓርቲዎቹ ውስጣዊ ዲሞክራሲን በሚያረጋግጥ መልኩ ተደራጅተዋል ወይ የሚለው ነው፡፡» ይላሉ፡፡ የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም (UNDP) በ**2006** «A HANDBOOK ON WORKING WITH POLITICAL PARTIES» በተሰኘ ርዕስ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ስለሚኖር አሰራር ጥናታዊ መጽሐፍ አዘጋጅቶ ነበር፡፡ እናም በዚህ መጽሐፍ ላይ በአፍርካ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያተኩረው የፕሮፌሰር ሳሊህ አጭር ጽሁፍ ተካትቶ ነበር፡፡ ፕሮፌሰሩም «The Challenges of Internal Party Democracy in Africa» በተሰኘው ጽሁፋቸው በአፍሪካ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የተንሰራፋውን የውስጣዊ ዲሞክራሲ ችግር ይዳስሳሉ፡፡

የአንድ ፓርቲ ውስጣዊ ዲሞክራሲ ለሁሉም የፓርቲ አባላት፣ ለህዝብ እና ለሀገር ጥቅም መቆምን እንደሚያመላክት የጠቆሙት ሳሊህ ውስጣዊ ዴሞክራሲ የፓርቲ መዋቅሮች እና አደረጃጀት ሁሉን አካታች እና አሳታፊዎች ናቸው ማለት እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ የፓርቲ አወቃቀር እና አደረጃጀት ሁሉን አካታች እና አሳታፊ መሆኑ ደግሞ «ለዲሞክራሲያዊ የፓርቲ አመራር እና እሴቶች መፈጠር እና መጉልበት መሠረታዊው ንጥረ ነገር ነው፡፡» ይላሉ፡፡ «በውስጣዊ አሰራራቸው ዲሞክራሲያዊ የሆኑ ፓርቲዎች ብዙሃኑን ሳገለለ የጥቂቶች የበላይነት ሳይሆን የቡድን እርምጃዎች አራማጆች ናቸው፡፡

የትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የአባልነት መስፈርቱ ወይም የኮሚቴ አወቃቀሩ በመደብ፣ በዘር፣ በጾታ ወይም በሀይማኖት ላይ በመመርኮዝ የተወሰኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚያገልል ከሆነ ዲሞክራሲያዊ ለመሰኘት ብቃት የለውም።»

ፕሮፌሰር ሳሊህ የፖለቲካ ፓርቲዎች በፓርቲው ሕግጋቶች ተመርተው ፓርቲውን እንደ ድርጅት እንዲያስተዳድሩ የተወሰኑ ሥልጣኖችን እና ኃላፊነቶችን ለተወሰኑ አመራሮቻቸው እና ኮሚቴዎቻቸው እንደሚሰጡ በመግለጽ፣ «ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ የፓርቲ አመራሮቹ የተሰጧቸው ኃላፊነቶች እና የመተግበሪያ መንገዶች መጠን እጅግ ሰፊ ይሆንና ሥልጣናቸውን አላግባብ እንዲጠቀሙ ያበረታታቸዋል።» ይላሉ። «ስለዝህም የፓርቲዎች ውስጣዊ አስተዳደር በዲሞክራሲያዊ ህብረተሰብ ውስጥ ከፍተኛ ጥንቃቄ ከሚጠይቁትና ከባድ ከሆኑት ትግበራዎች አንዱ ነው።»

በፓርቲዎች ውስጣዊ ዲሞክራሲ ላይ የሚያውጠነጥነው የፕሮፌሰሩ ጽሁፍ አጠቃላይ የአፍሪካ ፓርቲዎችን የሚመለከት ነው። በአፍሪካ የፓርቲዎች ውስጣዊ ዲሞክራሲን የሚያሰናክሉ እንቅፋቶች ቢያንስ ስድስት መሆናቸውን በመጠቆምና በመዘርዘር እንዲህ ያብራራቸዋል፡-

<u>**የልሂቃን ተፅዕኖ፡-**</u> ምንም እንኳ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአጠቃላይ የልሂቃን ተጽዕኖ የሚታይባቸው ቢሆንም በተለይ ግን በአፍሪካ ውስጥ በሚገኙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ ይህ በግልጽ ይታያል። ፖለቲካዊ ግንዛቤ አለመኖሩ በአንፃሩ በብሔርተኝነት፣ በሀይማኖት፣ ለፓርቲ በመስጠት፣ እና በመሳሰለት ላይ መሠረት ላደረገ ለፖለቲካ ሂደት ብዝበዛ የተመቸ ነው።

<u>**የአመራር መረጣና መተካካት፡-**</u> አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲ ውስጣዊ ሕግጋቶች መደበኛ እና ወቅቱን የጠበቀ የአመራር ምርጫ (ሹመት) ማካሄድን በግልጽ ያካተቱ ቢሆንም የፓርቲው መስራቾች (founding-fathers) ብዙውን ጊዜ በአመራርነት ይቀጥላሉ። ይኸውም ፉክክራዊ ፖለቲካን ያሰናክለዋል።

<u>**አድሏዊ የእጩዎች አመራረጥ፡-**</u> የተወሰኑ (ጥቂት) የአፍሪካ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሴቶችን እና በህብረተሰቡ ተጠቃሚነትን የተነፈጉ አናሳዎችን በሕግ አውጪው ለመወከል እና በምርጫ ፉክክር እጩ ተወዳዳሪ ለማድረግ የሚፈቅዱ ቢሆንም አብዛኞቹ ግን እነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች በማግለል ይታወቃሉ።

<u>**እከክልኝ-ልከክልህ ግንኙነቶች፡-**</u> በፖለቲካ ፓርቲ ውስጥ ጉልህ ኃይል ያላቸው ሰዎች እና ጥቂት ግለሰቦች ለፓርቲ አመራሮቹ የሚያቀርቧቸው መደለያዎች አመራሮቹ ፓለቲካዊ ልዩ መብቶችን ለማካበት የመንግስት ሀብትን እንደሚጠቀሙ የፓርቲ ጌቶች (bosses) ዓይነት ጠባይ እንዲኖራቸው ያደርጋሉ። የእከክልኝ-ልከክልህ ግንኙነቶች ብዙውን ጊዜ የሚዳብሩት አንዱ ወገን በፓርቲ አመራር መረጣ ላይ የአመራርነት ቦታው ሲሳካ ተከፋይ የሚሆን ውለታን በመጠበቅ ለሌላው ወገን ደምፁን ሲሰጥ ነው።

**<u>መደበኛ እና ወቅቱን የጠበቀ ምክክር አለመኖር፡-</u>** በፖለቲከኞች እና በፖለቲካ ፓርቲዎች መተማመንን ከማጣት ጋር በተያያዘ በመላው ዓለም ያለ ሂደት ነው፡፡ በአፍሪካ ሀገራት መካከል ሁኔታው የተለያየ ይሁን እንጂ በምርጫ ወቅት ብቻ መራጮችን ለመቀስቀስ ብቅ የሚሉ የፓርቲ ተወካዮች እና የኮሚቴ አባላት በምክክር (በስብሰባ) ላይ አለመገኘታቸው የተለመደ ነው፡፡

**<u>በፓርቲ የገንዘብ አስተዳደር ተጠያቂነት እና ግልጽነት አለመኖር፡-</u>** ልገሳዎችን፣ የምርጫ ቅስቀሳ ወጪዎችን እና የሂሳብ መዝገብ ኦዲትን ለመቆጣጠር ውስጣዊ የፓርቲ ሕጎች ሊኖሩ ቢችሉም የገንዘብ ልውውጦችን ለማመሳከር ከባድ ነው፡፡ እንዲሁም ልውውጡ ርዕዮተ-ዓለምን በሚደግፉ፣ ተከፋይ ውለታ በሚጠብቁ ወይም የፖለቲካ ህልማቸውን ለማሳካት በሚፈልጉት መካከል ድብቅ የሆኑ ግንኙነቶችን ያካትታል፡፡ በአብዛኛዎቹ የአፍሪካ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴያቸውን ለመደጐም ጥቂት ወሳኝ ግለሰቦችን ባቀፈ ቡድን ላይ፣ በነጋዴ ባለሀብቶች ላይ፣ ከሌላ ፓርቲ ጋር በሚኖር ቁርኝት ላይ፣ እንዲሁም በወንድማዊ ደርጅቶች ላይ ይመረኮዛሉ፡፡

ፕሮፌሰር ሞሐመድ ሳሊህ እነዚህ ከፊሎቹ ችግሮች የተሻሉ ሕጐችን በማውጣት፣ ዲሞክራሲያዊ እሴቶችን ተቋማዊ በማድረግ፣ እንዲሁም የማህበረ-ኢኮኖሚውንና የፖለቲካውን አጠቃላይ መንፈስ በማሻሻል ሊፈቱ እንደሚችሉ ይጠቁማሉ፡፡ የውስጥ ዲሞክራሲን ካለማስፈን ጋር በተያያዘ የአፍሪካ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሌሎች ጥፋቶቻቸው እንዳሉ ሆነው ወደታች በሚጐትቷቸው ሁኔታዎች ውስጥ እንደሚገኙም ጠቁመው ነበር፡፡- የተንሰራፋ ድህነት፣ አንፃራዊ የሆነ ከፍተኛ የፖለቲካ ግንዛቤ እጥረት፤ እንዲሁም ባላቸውና በሌላቸው፣ በገጠራማና በከተማ አካባቢዎች መካከል የሚገኝ ሰፊ የገቢ ልዩነት፡፡

በተጨማሪም «አብዛኛዎቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች አሁንም ድረስ የፖለቲካ አጀንዳዎቻቸው የእነርሱ አይደሉም፡፡» በሚለው ሀሳብ ጽሁፋቸውን ያጠቃለሉት ፕሮፌሰሩ «ዓለማቀፋዊ እሳቤ የሆነው ፓርቲን መሰረት ያደረገ ዲሞክራሲ ተግባራዊነቱ ፖለቲካን ለገበያው ተገዥ በሚያደርገው «ኒዮ-ሊብራል ግሎባላይዜሽን» ንፍቀ-ክበብ ውስጥ የተገደበ ነው፡፡ ይህ ኒዮ-ሊበራሊዝምን ከተቀናቃኞቹ (ኮሙኒዝም እና ወታደራዊ ሶሻሊዝም) በማግዘፍ የፖለቲካ ፓርቲ ርዕዮተ-ዓለሞችን የቀረፀ ብቻ ሳየሆን የትኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ላለመተግበር የማይቻለውን የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ፖሊሲ ማሻሻያዎች ይጭናል፡፡» ብለዋል፡፡

ፕሮፌሰሩ እንዳሉት እነዚህ ጥቂቶቹ ናቸው፤ ሆኖም በተወሰነ መልኩ የተለየ ገጽታ ሊኖራቸው ይችል እንደሆን እንጂ በሀገራችን የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚታየው የውስጥ ችግር ከላይ የተጠቀሱትንም ይጨምራል፡፡ ከዚህ ባለፈ ፖለቲካን አማራጭ መፍትሔ እንደማፈላለጊያ ሳይሆን እንደመተዳደሪያ የሚመለከቱ ግለሰቦች በአመራርነት

ቦታ ላይ መቀመጣቸው የሀገራችን ፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጣዊ ዲሞክራሲን እንዲያጡ መንገድ ይከፍታል:: ብዙ አባላቶች ያሉት ሆኖ በአንድ ግለሰብ ውሳኔ የሚንቀሳቀስ ፓርቲ በሀገራችን መንሰራፋቱ አይዘነጋም:: የፓርቲውን የገንዘብ አስተዳደር የሚወስኑ ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና ሌሎች አካላት በፓርቲው ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ያላቸው ተጽዕኖ የሀገራችን ፓርቲዎችን የውስጥ አሰራር ሲፈታተነው መመልከት ቀላል ነው::

ለወራት ያክል በነቆራና በውዝግብ ያለፈው የአንድነት ፓርቲ የውስጥ ችግር ጭራሽ እየባሰበት መጥቷል፤ የአንድነት ጉዳይ አደባባይ ወጣ እንጂ የስንቶቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች አመራር ስለዲሞክራሲ እየሰበከ በፓርቲው ውስጥ አምባገነናዊ እንደሆነ ትግበራዎች ያመላክታሉ:: እያንዳንዱ ፓርቲ በውስጥ አሰራሩ ዲሞክራሲን ካላሰፈነ፣ የሕግ የበላይነትን ካላከበረና ካላስከበረ፣ ለሰብዓዊ መብት ካልተጨነቀ ሀገርን የሚያህል ነገር ቢገጥመው ምን ሊሆን ነው?

# ከመብት ገፋፊው መብት አጋፋፊው

ታክሲ ውስጥ ነው:: የተለመደው የተሳፋሪ እና የወያላ የታሪፍ ክርክር ይሰማል:: «ትጨምር እንደሆነ ጨምር» ይላል ወያላው፤ ተሳፋሪው ደግሞ «ታሪፉ ይሄ ነው፣ ምን ታደርገኝ እንደሆነ እናያለን::» በጭቅጭቁ የታክሲ ሾፌሩም ይገባል፣ «ካልከፈልክ ውረድ፣ ምን ትጨቃጨቃለህ?» ይላል:: በዚህ መሃል የተጠየቀውን ሳያንገራግር የሚከፍል ሌላ ተሳፋሪም አይጠፋም፤ «ለጥቂት ሳንቲም ለምን ትጨቃጨቃለህ፣ ክፈለውና ሰላም ስጠን» በማለት ከጭቅጭቁ ጥልቅ ይላል:: ጉዳዩ የጥቂት ሳንቲም አለመሆኑን ያልተረዳ፣ ደግሞ ሌላ ሰላም ፈላጊ ተሳፋሪ «እኔ እሞላለሁ» ሲል ጭቅጭቁን ለማብረድ ይሞክራል:: ሾፌሩ ወደኋላ በመዞር «ካልከፈልክ መውረድ ትችላለህ፣ የአባትህ መኪና አደረከው እንዴ?» ለማለት አልፎ አልፎ መኪናውን ቆም ቢያደርግም ታክሲው ግን መሄዱን ቀጥሏል:: ወያላው እና ተሳፋሪው እርስ በርስ የሚመራወሯቸው ጸያፍ ስድቦችም ከታክሲው መስታውት ጋር ሲገጫጩ ይታያሉ:: ስድድቡ ወደ ግብግብ ሊያመራ እንደሚችልም ይገመታል::

ከላይ የተቀመጠውን ትዕይንት ያልታደመ የታክሲ ተጠቃሚ አይኖርም፤ ይህ የቀን ተቀን የታክሲ ውስጥ ድራማ ቁንጽል ስለመሆኑም እርግጥ ነው:: እርሶም የታክሲ ትራንስፖርት ውጣ ውረዱን በቅርበት ያውቁታልና ከላይ በተገለጸው ትዕይንት ውስጥ ሰናይ ገጸ ባህሪ የሚሉት የትኛውን ይሆን? ከታክሲ ተሞክሮት አንፃር የትኛው ገጸ ባህሪ ይወክሉት ይመስሎታል?

የዚህ ጽሁፍ ዓላማ የተለመደውን የትራንስፖርት ችግር ማስተጋባት ብቻ አይደለም፤ ይልቁንም የታሪፍ ጭቅጭቅ የመብት እንጂ የጥቂት ሳንቲም ጉዳይ አለመሆኑን ለማስገንዘብ ነው::

ከታሪፍ ባሻገር በታክሲ ትራንስፖርቱ የሚስተዋሉ ችግሮች አሸን ናቸው:: እያቆራረጡ መጫን ተሳፋሪን ያማረረና እላፊ ወጪ የሚጠይቅ የታክሲዎች ተግባር መሆኑን ማንም አያጣውም:: ከሁሉም በላይ ደግሞ በመስመራቸው አልፈውት የሚሄዱበት ቦታ ለመድረስ የሚፈልግን ተሳፋሪ አልጭንም ማለታቸው ብዙዎችን ሲያንገላታ እንመለከታለን:: ለምሳሌ ወደ አምባሳደር ለመሄድ ኦሎምፒያ አካባቢ ቆሞ ታክሲ የሚጠብቅ ሰው አማራጩ ከቦሌ-ፒያሳ የሚሄድ ታክሲ ቢሆንም ወያላዎቹ ግን «ፒያሳ ብቻ» ሲሉ ይደመጣሉ:: ይኼን ጊዜ ሴቶች፣ አቅመደካሞች እና የታክሲ ውስጥ ንትርክ የመረራቸው ተጠቃሚዎች ከመግባት ይቆጠባሉ፤ ወይም የፒያሳ ሂሳብ (ጊዜያዊ ቢሆንም ብር 2.40) ከፍለው ይጓዛሉ:: አንዳንዶች ደግሞ ቀጥ ብለው በመግባት የአምባሳደር ሂሳብ (0.90 ሣንቲም) ይከፍላሉ፤ ታዲያ ጭቅጭቁ አይቀሬ ነው:: በርግጥም ወያላዎቹ እንደሚሉት ላያዋጣቸው ይችላል:: ነገር ግን «አምባሳደር» የሚል ታክሲ እስኪመጣ በፀሃይ መንቃቃት፣ ወይም በታሪፉ ላይ ጨመሮ መክፈል ተሳፋሪውን ያዋጣዋል ማለት አይደለም፤ የአዋጪነት ጉዳይ ሊነሳ ባይገባም::

የታክሲ ትራንስፖርት ችግር ተዘርዝሮ አያልቅም:: ምግባረ ሰናይ የሆኑ አሽከርካሪዎች እና ወያላዎች መኖራቸው የማይካድ ሆኖ የመኪናቸውን አገልግሎት ሰጪነት የሚዘነጉ አያሌ መሆናቸው ችግሩን ያባብሰዋል:: ምናልባትም ይህ ላያስገርመን ይችላል፤ አንዳንድ ተሳፋሪዎች ከወያላው ይበልጥ ሊያብከነክኑን የሚችሉበት ሁኔታ ያጋጥመናልና::

ከመግቢያችን ላይ ባስነበብናችሁ ትዕይንት ውስጥ የተመለከታችኋቸው ሁለት ተሳፋሪዎችን ልብ በሏቸው:: «ለጥቂት ሳንቲም ለምን ትጨቃጨቃለህ፣ ክፈለውና ሰላም ስጠን» በማለት በጭቅጭቁ ጥልቅ ያለውንና «እኔ እሞላለሁ» ሲል ጭቅጭቁን ለማብረድ የሞከረውን ማለታችን ነው:: እንዲህ ያለ ተሳፋሪ ሲያጋጥሞት እንዴት መልሰውት ይሆን?

የቅድሙን ምሳሌ እንድገመውና፣ «ፒያሳ ብቻ» እያለ በሚጠራ ታክሲ ውስጥ አምባሰደር ሊሄድ ዘው ብሎ የገባ ተሳፋሪ ከወያላው ጋር ውዝግብ ውስጥ መግባቱ አይቀሬ ነው:: 0.90 ሣንቲም ሲከፍል «ጨምር» ይባላል፤ እርሱም «አምባሳደር ነኝ» ይላል:: ይሄን ጊዜ «ፒያሳ ብቻ እንደምጭን ተናግርያለሁ» ይላል ወያላው:: ታዲያ በዚህን ሰዓት «አዎ፣ ተናግሯል» የሚል ተሳፋሪ ሲያጋጥም ከመብት ገፋፊው መብት አጋፋፊው አልባሰም ይላሉ? መብትን አለማስከበር አንድ ነገር ነው፣ ሌላ ሰው መብቱን እንዳያስከብር ማድረግ ግን የባሰው ይሆናል::

## ሞቲቬሽን

# ከደስታ ጋር መላመድ

ከየት የመጣ ነው ይሄ ሁሉ ደስታ? ያለማቋረጥ ሁሌ ከየት እየተገኘ ነው? ደስታው መኖሩ ብቻ ሳይሆን እለት ከእለት እየጨመረ የሚሄደውስ ከምን የተነሳ ነው? ይሄ ነገር የተወሰነ ቦታ ላይ የሚገኝ ነገር ነው ወይስ?

እሷን በደንብ ላስተዋላት ሁልጊዜ ተመሳሳይ የሆነ ባህሪይ ታሳያለች:: እንደ ሌላው ሰው ችግር ቢያጋጥማትም ፊቷ ግን ሁሌ በደስታ እንደተሞላ ነው:: እንደውም ይህችን ሴት ጠጋ ብሎ ላናገራት ሁሉ ነገር በሽ በሽ ያላት ይመስላል:: እውነታው ግን ሌላ ነው:: ምናልባት ለእኔ ይበቃኛል የምትለውን ያህል ይኖራት ይሆናል ወይም ከዛም ያነሰ:: ምናልባትም ደግሞ ካሰበችውና ከምትፈልገው በላይም ሊኖራት ይችላል:: ነጥቡ ግን እሱ አይደለም:: በምንም ነገር ሊለካ የማይችለውን ደስታ ሁልጊዜ ይህቺ ሴት ካላት እና ከሰጠች ያንን ማድረግ ፈቅዳ ነው ማለት ነው:: ደስታ ሆኖ ናልኝ ተብሎ ተመርጧል:: ድርጊቶች ሁሉ ላይ ትልቅ ኃይል ያንፀባርቃል:: በደስታ ህይወትን መምራት፣ በደስታ ቤተሰብን መምራት፣ በደስታ ስራን መስራት፣ በደስታ መዝናናት፣ በደስታ ንግግር ማካሄድ፣ በደስታ ችግርን መፍታት፣ በመሳሰሉት ማንኛውም ነገሮች በዚህ ጥሩ ስሜት ውስጥ የበለጠ ይመቻቸዋል ማለት ነው::

ግን ሁልጊዜ እንደዚህ ዓይነት ጥሩ ስሜት ውስጥ ለመሆን ምን ያስፈልጋል? ይሄ ስሜት ከውስጣችን ያለ ስለሆነ ከውጪ የምንጨምረው ሌላ ምንም ነገር የለም:: ግን ከውስጣችን ተጨማሪ ማድረግ ያለብን ነገር አለ:: ምንም እንኳን በውስጣችን ከእኛ አልፎ ተርፎ ለሌላም መትረፍ የሚችል የደስታ ነፀብራቅ የሚሆኑ ስሜቶች ቢኖሩንም ሁሌ እያስታወስን እነዚህን ስሜቶች ለማውጣት፣ ለማንፀባረቅ፣ ለማሳየት እና ለመሆን መጣር አለብን:: ለዛ ነው ሁሌ ደስተኛ የሆነ ሰው ሲያጋጥመን ያ ሰው ደስተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ልንገነዘበው የሚገባን ሆን ብሎ ደስተኛ ለመሆንም ጭምር እየጣረ መሆኑ ነው:: ይሄ ጥረት እንደማንኛውም ስራ ሊቆጠር ይችላል:: ከሌሎች ስራዎች የሚለየው ግን ደስተኛ መሆን ልምድ እስኪሆን ድረስ መጣር ያስፈልጋል እንጂ አንዴ ደስተኝነት ልማዳችን ከሆነ ከዛ በኋላ ስራ አይጠበቅብንም:: ልክ እንደማንኛውም ልምድ አንዴ ውስጣችን ከገባ ያ ነገር ከእኛ ለመለየት ይቸግረዋል:: እኛም ያንን ልምድ ለማንፀባረቅ አይከብደንም:: ይሄም ልምድ ተፈላጊም፣ ተወዳጅም፣ አገልግሎት ሰጪም ይሆናል:: ሁሌ ደስታን የሚያንፀባርቅ ሰው ተፈላጊ ሰው ነው:: በተጨማሪም ያ ሰው ተወዳጅ ነው:: ከሁሉ የሚበልጠው የደስታ ጥቅም ግን ከራሱ እና ከባለቤቱ ውጪ ወጥቶ የሚሰጠው ወይም የሚያመጣው ውጤት ነው:: በደስታ የሚደረግ ማንኛውም ድርጊት የጥሩ ውጤት የማምጣት ዕድሉ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው::

**ሆን ብዬ ነው . . .**

ስሟ ደስታ ባይሆንም ሁሉም ግን ደስታ ብሎ ነው የሚጠራት፡፡ እሷ ያለችበት አካባቢ ያንን ደስታ አለመጋራት እጅግ ይከብዳል፡፡ ትንሹንም ትልቁንም ስራ በሚያስቀና ደስታ ነው የምታከናውነው፡፡ ሁሉንም ሰው የሚለቅ በማይመስል ፈገግታ ነው የምታናግረው፡፡ የዚህች ሴት የቀረበ ጓደኛ የሁልጊዜ ድርጊቷን ታያለች፡፡ ጓደኛዋ በአጠገቧም ትለፍ ወይም በሩቁ ውስጧ ያላት ኃይል ሁሌ እንዳስገረማት ነው፡፡ የምትነካቸው ነገሮች ላይ ሁሉ መዳከም፣ መሰላቸት እና ችላ ባይነት በጭራሽ አይታይም፡፡ ይህቺ ሴት የጓደኛዋን ሁኔታ ስታስተውል ከመገረምም አልፋ ራሷን ጠየቀች፡፡ «ይህቺ ጓደኛዬ ሁሌ እንዴት ደስተኛ ትሆናለች? ከእኔ የበለጠ ምን ስላላት ነው? ወይስ እኔ ምን የጐደለኝ ነገር አለ? እንደውም እውነቱን በደንብ ካሰብኩት እኔ ከእሷ በበለጠ የገንዘብ ሀብት አለኝ» ብላ አሰበች፡፡ እናም ይህንን የከነከናትን ጥያቄ ጠየቀቻት፡፡

«ሁሌ ደስተኛ እንዴት ልትሆኚ ቻልሽ?»

«አንቺ ለምን አይደለሽም?»

«እኔማ እንደየሁኔታው ደስተኛ ልሆንም ላልሆንም እችላለሁ፣ ሁኔታዎች የእኔን ባህርይ ይወስኑታል፡፡ አንቺ ግን ሁሌም ተመሳሳይ ነው ባህሪሽ፡፡ ይሄ እንዴት ሊሆን ቻለ?»

«እኔ ጋር እንደየሁኔታዎች የሚባል ነገር የለም፡፡ ስሜትን በተመለከተ መርጬ የማደርገውና የምሆነው ነገር ነው፡፡ አንቺ ያልሻቸውን የተለያዩ ሁኔታዎች በደስታ ለመጋፈጥ ነው የመረጥኩት፡፡ ስለዚህ ሆን ብዬ ነው ደስታን የመረጥኩት፡፡ »

እና ይህቺ ደስታ ተብላ የምትጠራው ጓደኛዬ በድርጊቷ ደስታ እንደተባለች ሁሉ እኔ ምን እየጠበቅኩ ነው? አልኩ፡፡ ደስታ ሁላችንም ውስጥ ቢሮም እሷ ግን አስባበት ያን ባህሪይ እንደምታንፀባርቅ ተረዳሁ፡፡

ሁላችንም ብንሆን አስበንበት ይሄንን ጥሩ ባህሪይ ካልፈለግነውና ካልሆነው የሆነ ዓይነት ባህሪይ ማሳየትና ማንፀባረቅ ስላለብን ሌላ ዓይነት ባህርይ እናሳያለን፡፡ ስለዚህ አስበንበት ደስተኞች እንሁን፣ ይህ ባህሪይ እየቆየ ሲሄድ ልምድ ይሆንብንና ከዛ የተለየ ባህሪይ ለማሳየት አስቸጋሪ ይሆንብናል፡፡ የሚፈለገውም ይሄ ነው፡፡

# ስፖርት/ኪነጥበብ

## የመርዓዊ ሌላው ዓለም «ስፖርት»

### «የስፖርት ጋዜጠኞች የመንፈስ ባንዳ እየሆኑ ህዝቡንም ባንዳ እያደረጉት ነው»

**<u>አቤል ዓለማየሁ ብዙ ከተባለለት የመርዓዊ ስጦት የጥበብ ህይወት በላይ ያልተነገረውን ከስፖርት ጋር ያላቸውን ጥምረት በተከታዩ ፅሁፍ በጉልህ ለማሳየት ሞክሯል።</u>**

*ጌታቸው መኩሪያን አንስቶ ሳክስፎንን መዘንጋት አይታሰብም። ስለ አየለ ማሞ የሚያወሳ የጨዋታውን ጠርዝ ከ«ማንዶሊን» መጀመሩ አይቀርም። በ1928 ዓ.ም. ወሎ አምባሰል ውስጥ የተወለዱት አንጋፋው አርቲስት መርዓዊ ስጦታን አንስቶም **ክላሪኔትን** መርሳት አይቻልም። ብዙዎች «መርዓዊ ማለት ክላሪኔት፤ ክላሪኔት ማለት መርዓዊ ነው።» ይላሉ። እርሳቸው ግን በዚህ በፍፁም አይስማሙም። «አምባሰልና ትዝታን በክላሪኔት መጫወት እኔ ልጀምረው እንጂ ያስተዋወቀው "ወዳጄነህ ፍልፍሉ" ነው» ሲሉ ዛሬ በህይወት የሌሉትን የቀድሞ የብሔራዊ ቲያትር ቤት ባልደረባቸውን ያስቀድማሉ።*

*መርዓዊ የክላሪኔታቸውን ቁልፍ እየነካኩ አምባሰልን ሲጫወቱ የማይሸነፍና እጅ የማይሰጥ ልብ አይኖርም። እሳቸው ሲጫወቱ እንባ የሚቀድማቸውም አሉ። በአንድ ወቅት አሜሪካ ኬኔዲ ማዕከል ውስጥ ጥላሁን ገሠሠን ጨምሮ ከሃያ በላይ የኢትዮጵያ የሙዚቃ ባለሙያዎች በተገኙበት መድረክ አምባሰልን ሲጫወቱ አዳራሽ ሙሉ ህዝብ እንባውን ያንቆረቁረው እንደ ነበር ይገልፃሉ። «አምባሰል በራሱ የመንዘር ኃይል አለው። ትዝታንም እወዳለሁ፤ እጫወታለሁም። ነገር ግን እንደ አምባሰል የሚማርከኝ የለም። የሀገሬም (የትውልድ ቦታ) ዜማ ስለሆነ ጥሩ እጫወተዋለሁ ብዬ አስባለሁ።» የሚሉት የሙዚቃ ባለሙያ «አምባሰል በመርዓዊ ጥዑም ነው ይባላል ምክንያቱ?» ብላችሁ ብትጠይቋቸው «ሁለት ጥሩ ዶሮ ወጥ የሚሰሩ ሴቶች ቢኖሩ የአንዷ ይበልጥ መጣፈጡ አይቀርም» ሲሉ ንፅፅሩን በምሳሌ ያስረዳሉ።*

*መርዓዊ የጥሩ አባት ምሳሌ ይመስላሉ። ላገኛቸው ሁሉ ፈገግታ ቸረው በፍቅር ሰላምታ መስጠቱን ተክነውበታል። «የኔ ልጅ» የሚል ቃል በአፋቸው ሙሉ ነው። ይህን ቃል የሚጠቀሙት ለስጋ ልጆቻቸው ብቻ አይደለም። ለሙያ ልጆቻቸው፣ በዕድሜ ለሚያውቋቸው ታናናሾቻቸውና ሰላምታ ላቀረበላቸው ሁሉ ቃሏን አይሰስቱም። አንባቢ ናቸው። የሳምንቱን ጋዜጦች በትኩረት ይከታተላሉ። «ጋዜጣችሁን (ሰውራምባ ታይምስ) በጣም እወዳታላሁ፤ አደንቃታለሁም። ደፋርና ህዝባዊ ነች። የጋዜጣ ሱሰኛ ስለሆንኩ ማክሰኞ ጠዋት አታልፈኝም። የቡናና የጋዜጣ ሱስ አንድ ነው።» ሲሉ የማንበብ አምሮታቸው እስከ ምን እንደሆነ ነግረውናል።*

*የኢትዮጵያ ሙዚቃ ውስጥ አስረጂ መሆን የሚችሉ አንጋፋ ባለሙያ ናቸው። ስለ ሙዚቃችን ምርምር ለማድረግ የሚሞክር ሁሉ መረጃ ለመጠየቅ የመርዓዊን በር ማንኳኳቱ የተለመደ ነው። መርዓዊ ስለ ትላንት የኢትዮጵያ የሙዚቃ እውነቶች ሲገልፁና ሲያስረዱ ኖረዋል። መርዓዊን አሳድዶ ያላገኘ የመገናኛ ብዙሐን የለም። ሁሉም የጥበብ ህይወታቸውን ተርከዋል። የመርዓዊ ያልተነገረና ያልተወራ ሌላ ዓለም ግን አለ፤ ስፖርት።*

መርዓዊ በስፖርት ውስጥ ተሳታፊ አልነበሩም:: የማየት ግን ሱሰኛ ናቸው:: ሀገራችን አዘጋጅታ ዋንጫ ያነሳችበትን 3ኛውን የአፍሪካ ዋንጫ በትኩረት ተከታትለዋል:: የካምቦሎጆ ደንበኛ ያደረጋቸው ሀገራችን በግብጽ ላይ የበላይነቱን ወስዳ ዋንጫ መሳሟ ነው:: የወቅቱ የኢትዮጵያ ብ/ቡድን አሰልጣኝ የነበሩት ይድነቃቸው ተሰማ ቡደኖች በአውሮፓና በሌሎች ሀገሮች ለልምምድና ለወዳጅነት ጨዋታዎች እንዲሄዱ ማድረጋቸው የወቅቱ የቡድኖች ጥንካሬ እንደነበር መርዓዊ ያምናሉ::

መርዓዊ ስለ እግር ኳስ ሲያወሩ የእግር ኳስ ተንታኝ (Football Analyst) ያህል ጥልቅ እውቀት አላቸው:: «ጥሩ ጥሩ ተጨዋቾች ኖረውህ ብቁ እውቀት ያለው አሰልጣኝ ከሌለህ ዋጋ የለህም:: ለስፖርቱ ትኩረትም ወሳኝ ነው:: ከእኛ በኋላ የተነሱ ሀገሮች እግር ኳሳቸው ያደገው የዓለማችንን ታላላቅ አሰልጣኞች ስለቀጠሩና ዓለም የደረሰበትን የአሰለጣጠን ዘይቤ ስለተከተሉ ነው:: ሱዳን ነፃ የወጣችበትን ሁለተኛ ዓመት ስታከብር ሄጄ ነበር:: የአል-ሜሪክ፣ የአል-ሂላልና የብሔራዊ ቡድኑ፤ ሦስት ብቁ ስታዲየም አላቸው» ሲሉ በንጽጽር የኢትዮጵያ እግር ኳስ የመሰረታዊ ነገሮች «ጠኔ» እንዳለበት ያመላክታሉ::

## ካምቦሎጆ አመለጠን

በቻይና መንግስት እርዳታ በኢትዮጵያ ሊሰራ የነበረ ስታዲየም መኖሩ ከአስራ አምስት ዓመታት በፊት ይነገር ነበር:: ወሬው ግን ህልም ሆኖ ቀረ:: የኢትዮጵያ መንግስት «የሚያስፈልገን ማዳበሪያ እንጂ ካምቦሎጆ አይደለም» በማለቱ የግንባታው ወሬው «ወሬ» ሆኖ ቀረ:: ይህ መርዓዊን ያንገበግባቸዋል:: በቅርቡ ግብፅና አልጄሪያ የዓለም ዋንጫ ትኬትን ለመቁረጥ ሱዳን ውስጥ በገለልተኛ ሜዳ ያደረጉት ጨዋታ «ኢትዮጵያ ብቁ ሜዳ ቢኖራት እድሉን መጠቀም ያስችላት ነበር» ብለው በቁጭት ላይ ቁጭት እንዲደርቡ አድርጓቸዋል::

## ጀግኖችን የመርሳት አባዜ

ለኢትዮጵያ ታላቅ ታሪክ ያስቀመጡ ጀግኖችን መንከባከቡ ላይ ጥሩ ስም የለንም:: አጋጣሚ ከተገኘም ለማጠልሸት እንቀድማለን:: «መርሐዊ ስጦት የሚገባቸውን ክብር አግኝተዋልን?» ብለን ብንጠይቅ «በሚገባ» የሚል መልስ ለመስጠት የመንፈስ ጥንካሬ ማግኘት ከባድ ነው:: መርዓዊ በበኩላቸው የአፍሪካ ስፖርት አባት ተብለው የሚሞካሹት ይድነቃቸው ተሰማ ለሀገራቸው እግር ኳስ ቢተጉም ዛሬ የሚታወሱበት ቋሚ ነገር ስላልተቀመጠላቸው ሁሌም ቅር ያሰኛቸዋል:: «በቅ/ጊዮርጊስ ክለብ ጽ/ቤት ውስጥ አንድ ግለሰብ ካሰራላቸው ሀውልት በስተቀር ምንም መታሰቢያ የላቸውም:: ሞሮኮ ውስጥ ግን በስማቸው ስታዲየም ተሰይሟል:: ይህ እንዴት በሀገራቸው ማሳካት ያቅተናል?» ሲሉ ታላቁ የክላሪኔት ተጨዋች ይጠይቃሉ::

## ጥቁር ትዝታዎች

ባለፈት ሁለት ዓመታት በኢትዮጵያ እግር ኳስ ውስጥ ተፈጥሮ የነበረው መጥፎ ክስተትን «ብሔራዊ ስሜትን የሚገድል» ሲሉ መርዓዊ ይገልፁታል:: ተፈጥሮ በነበረውም ሁኔታ ከልብ አዝነዋል:: «ትምክህተኞች በፈጠሩት ችግር ሀገር እስከ መታገድ መድረሷ ያንገበግባል::» ሲሉ ሀዘናቸውን ይገልፃሉ:: የሚፃፉም ሆነ የማይፃፉ እግር ኳሳዊ ምልከታቸው የስፖርት ቅርበታቸውን ጥልቅ መሆኑን ያሳያል::

«የኢትዮጵያ ቡድኖች በሀገር ውስጥና በውጪ ተጨዋቾችና አሰልጣኞች ሊጠናከሩ ይገባል:: ተጨዋቾቻችን ውጪ ሀገር መጥተው መጫወት እንዳለባቸው ጭንቅላታቸውን አሳምነው መጣር አለባቸው:: አለበለዚያ እዚህ እርስ በራሳችን ጭቃ ብናቦካ ዋጋ የለውም» የሚሉት መርዓዊ ይቀጥላሉ «አሰልጣኞቻችን ትምክህተኝነት ያጠቃቸዋል:: ተጨዋቾቻችን ትንሽ ጭብጨባ ያደነዝዛቸዋል:: እኛምጋ (ሙዚቃ ውስጥ) ይህ አለ:: አስተማሪያችን የነበሩት ሙሴ ነርሲስ ናልባልዲያን አንድ ሙዚቀኛ ዘግይቶ ከመጣ «ትላንት ተጨብጭቦለት ነበር?» ብለው ይጠይቁ ነበር:: ጭብጨባ ገዳይ ነው::»

«ትላንት የተቋቋመው ሰበታ ከነማ ከትልልቅ ቡድኖች ጋር ተፎካካሪነቱን እያሳየ የመጣው ድርጅታዊ መዋቅሮቹን በማጠናከሩ ነው:: ማንቼስተር ዩናይትድ ክርስቲያኖ ሮናልዶን መልቀቁ ጉዳት እንዳስከተለበት ተመልክተናል:: በተጨዋቾች ላይ እምነት ማሳደር ይገባል::» ይላሉ:: «ተጨዋቾቼን ወሰዱብኝ» ብሎ ማማረርን ከዘመናዊ የእግር ኳስ ፍልስፍና ጋር የሚጋጭ ይሉታል:: «ተጨዋቹም ክለቦችም መጠቀም አለባቸው::» ይላሉ::

ከአበበ ቢቂላ አንስቶ እስካሁን ያሉትን የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ጀግኖች የማንቆለጳጵስበት ቃላት የለኝም እንደሚያጥራቸው ያወጋሉ::

## ስሙኝ

«የእግር ኳስ ሜዳዎች (መዘውተሪያ ቦታዎች) ካልተገነቡ፣ ተጨዋቾች ከስር ተኮትኩተው የሚመጡበት የተስተካከለ መንገድ ካልተዘረጋ፣ የአሰልጣኞቻችን አሰለጣጠን ተፈትሾ ዘመናዊነትን እንዲላበስ ካልተደረገ ዋጋ የለውም» ይላሉ:: በማስረጃነት የሚያቀርቡት ሀለማያ ዩኒቨርስቲ የሚያስተምሩት ዶ/ር ሞላ ዶዬ በአንድ የሬዲዮ ፕሮግራም ላይ ገብተው የተናገሩትን አስተያየት መስማታቸው ነው:: «አንድ ተጨዋች የጤንነት ምርመራ ሳይደረግለት አሸዋ እያሸከሙ በየተራራው ላይ አስሩጦ ውጤትን አገኛለው ማለት የዋህነት ነው» የሚለው የዶ/ሩ ንግግር ተገቢ መሆኑን ተስማምተዋል:: «እንዲህ አይነት ባለሙያዎች ያስፈልጉናል:: በአትሌቲክሱ ውጤት የመጣው እንደ ዶ/ር ወ/መስቀል ኮስትሬ አይነት ሳይንሳዊ ስልጠናን ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ሰላለ ነው» ሲሉ ይሞግታሉ:: አሰልጣኞች በውጪ ሀገር በቂ ስልጠና አግኝተው

የሚመጡበት ሁኔታ መመቻቸት እንዳለበትና ፍትሐዊ ዳኝነትን የሚያውቁ አርቢትሮች በባትሪ መፈለግ እንዳለባቸው ገልፀዋል፡፡

## የመርዓዊ አሁን

አርቲስት መርዓዊ ስጦት የኢትዮጵያ እግር ኳስ በየጊዜ እየወረደ እንደሄደ ቢያምኑም አሁንም ቢሆን አልፎ አልፎ ካምቦሎጆ መታደማቸውን አላቆሙም፡፡ የቅ/ጊዮርጊስ ክለብ የልብ ደጋፊ ናቸው፡፡ የክለቡ ደጋፊዎች የሚያቀነቅኑትን «ህዝባዊ ቡድናችን» የሚለውን ዜማ የደረሱትም እሳቸው ናቸው፡፡ በአሁን ጊዜ የስፖርት አፍቃሪውና ጋዜጠኞች ወደ አውሮፓ ሊጐች ማተኮር የሀገራችን የእግር ኳስ እንቅስቃሴ የመግረክ አቅሙ መዳከም መሆኑን ቢያምኑም እድገት እንዲኖር መሸሽ መፍትሄ አለመሆኑን ይገልፃሉ፡፡ «ሁሉም የሀገርን እግር ኳስ ለመታደግ ብሔራዊ ስሜት ኖሮት ሊሰራ ይገባዋል» የሚል መልዕክት አላቸው፡፡ «የእንግሊዝ ኳስ ተጨዋቾች የበሉትና የጠጡት ሳይቀር ከጠዋቱ 1:15 ጀምሮ ትሰማዋለህ፡፡ ጋዜጦች በየቀኑ ይሄን በፊት ገፃቸው ይደሰኩራሉ፡፡ ይህ ምን ማለት ነው?፡፡ ከአዲስ አበባ መቀሌ ድረስ በመኪና ተጉዘው ሰውነታቸው ዝሎ የሚጫወቱ ተጨዋቾች ውጤት ሊነገርላቸው ይገባል፡፡» ሲሉ ሁሉም ባለ ድርሻ አካላት ሀላፊነት እንዳለባቸው ይገልፃሉ፡፡ ነገሮችን በጥልቀት የሚመለከቱት መርዓዊ ሌላም የሚያስገርማቸው ነገር አለ፤ «እግር ኳስን በሬዲዮ» የተሰኘው ፕሮግራም፡፡ «እግር ኳስን በሬዲዮ» ጋዜጠኛ መሰለ መንግስቱ በፊት በሸገር ኤፍ ኤም በአሁኑ ሰዓት ደግሞ በፋና ኤፍ ኤም ላይ በተለይ የእንግሊዝ ፕሪምየር ሊግን ጨዋታዎችን ኮሜንትሪ የሚሰራበት (በቀጥታ የሚያስተላልፍበት) ፕሮግራም ነው፡፡ «መሰለ የእያንዳንዱን ተጨዋች ታሪክ ከቅደመ አያቱ ጀምሮ ይተነትነዋል፡፡ አንድ ቀን ምናለ የሀገሩን ተጨዋቾች ታሪክ እንዲህ ቢተንተን? ምናለ ለወገኑ መስራት ቢችል? ይሄ እኮ ብሔራዊ ስሜት ያለ መኖር ነው፡፡» የሚሉት አንጋፋው አርቲስት የውጪ ስፖርት ዲስኩር መብዛቱን በእጅ አዙር ቅኝ መገዛት እንደሆነ ይቆጥሩታል፡፡ «የስፖርት ጋዜጠኞቹ የመንፈስ ባንዳ እየሆኑ ህዝቡንም ባንዳ እያደረጉት ነው፡፡» ይህ ሊታረም ይገባል፡፡ ብሔራዊ ስሜት ሊኖረን ይገባል፡፡ በቅድሚያ ማክበር የራስን ልጆች ነው» በማለት ይናገራሉ፡፡

በቅርቡ በሀገራችን ቆይታ አድርጎ ለሄደው የዓለም ዋንጫ ነበረው ሽር ጉድ አልጣማቸውም፡፡ ከዋንጫዋ ጋርም ፎቶ የመነሳቱ ሂደት በሰው ዕቃ የማጌጥ ያህል ተሰምቷቸዋል፡፡ «ዋንጫው ለእኛ ትርጉም ይሰጥ የነበረው በዓለም ዋንጫ መካፈል ችለን የነበረ ቢሆን ነው» ይላሉ፡፡

## ያጋደለ ሚዛን

መርሐዊ ስጦት 43 ዓመት ሙሉ ከመድረክ ሳይለዩ ሙዚቃ ተጫውተዋል፡፡ መድረክን «መቅደሴ» ይሉታል፡፡ ጡረታ ከወጡ በኋላ 40 ለሚጠጉ ሙሽሮች በነፃ

መለያቸው የሆነችው ክላሪኔታቸውን ሰድረው አምባሰልና ትዝታን አንቆርቁረዋል፡፡ «ለሙዚቃ ሙሉ ዕድሜዬን ከመስጠቴም በላይ ልበ በሽተኛ ሆኛለሁ፡፡» ሲሉ ልባቸው ውስጥ በገባ ባትሪ (ፔስ ሜከር) የሚንቀሳቀሱት መርሐዊ የከፈሉትን መስዋዕትነት ይገልፃሉ፡፡

በ1986 ዓ.ም. ጡረታ ሲወጡ ይከፈላቸው የነበረው 390 ብር ነበር፡፡ እንደ መርሐዊ አባባል ጡረታ ሊወጡበት የቻሉበት ምክንያት ጥላሁን ገሠሠ በአንገቱ ላይ ጉዳት ከደረሰበት በኋላ መትረፉን አስመልክተው «የሙዚቃው ንጉስ» በሚል የደረሱት ግጥም፤ ዜማ ከተሰራለት በኋላ እንዳይተላለፍ መከልከሉ «ለጥላሁን ያልሆነ መድረክ ለኔ ምንድን ነው?» በማለት እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ በመበሳጨትም ከመጠን በላይ ሁለት አይነት መድኃኒት ውጠው ከሞት ጋር ግብ ግብ ገጥመዋል፡፡ ሦስት ቀን ምንም ሳያውቁ «ኮማ» ውስጥ ነበሩ፡፡ «ከሦስት ቀን በኋላ ስነቃ ከእንቅልፍ የመነሳት ያህል ነው፡፡ ዶክተሮች ጉበቱ ፈርሷል ብለው ቢያስቡም ተርፌያለሁ» የሚሉት መርዓዊ በቀጣይ ጊዜያት አሜሪካ ሄደው ህክምና አግኝተዋል፡፡ የህክምና ወጪያቸውን የሸፈኑት ሼህ መሀመድ አላሙዲ ሲሆኑ ያሉበትን ሁኔታ በቅርበት በማስረዳት የህክምና እድሉን እንዲያገኙ ያመቻቸላቸው በፍቅር የሚወዳቸውና የሚወዱት ጥላሁን ገሠሠ ነበር፡፡

የጡረታ ገቢያቸው የሃምሳ ብር ጭማሪ አድርጋ አራት መቶ አርባ ብር (440) ላይ ቆማለች፡፡ (43 ዓመት የመድረክ ውሎና 440 ብር?) የኑሮ ውድነት የብዙሐኑን ሆድ ባስባሰበት በዚህ ወቅት ያለ ተጨማሪ ገቢ በ440 ብር መኖር የማይታሰብ ነው፡፡ «እነ አቶ አብነት ገ/መስቀል ይረዱኛል፡፡ ያ ባይሆን ሳምንት መኖር ባልቻልኩና ባልፈለግኩ ነበር» ሲሉ ኑሮን በጡረታ ብቻ «የማይታሰብ» ይሉታል፡፡ «ሞትን እንደ ትልቅ ፀጋ እቆጥረዋለሁ መቸገርን ግን አልወድም፡፡ ሁለት ቀን በከፍተኛ ችግር ውስጥ ከመኖር አለመኖርን እመርጣለሁ፡፡ እግዚአብሔርም ይህን ተመልክቶ ደጋፊ ሰጥቶኛል፡፡» ይላሉ፡፡ ስዊድን፣ ቤልጂየምና አሜሪካ 3 ልጆቻቸውና አንድ የልጅ ልጃቸው ይገኛሉ፡፡ እነሱም ኑሮን ሊያግዟቸው ተዳርሰዋል፡፡

የመርዓዊ ጤንነት አሁንም የተሟላና አስተማማኝ አይደለም፡፡ ጡረታም ቢወጡ ዘወትር ሳይሳለሙት የማያድሩትን የብሔራዊ ቲያትር ደረጃን መሰል ቦታዎችን ሲወጡ ልባቸውን ያፍናቸዋል፡፡ በኢንዶግራፊ ታይተውም የደም ዝውውራቸው ደከም እንደሚል ተነግሯቸዋል፡፡ «ያ እንዲወገድ ኦፕሬሽን ማድረግ አለብኝ፡፡ በዚህ ዕደሜዬ (74) ልብ ኦፕራሲዮን ማድረግ አስቸጋሪ ስለሆነ ከበሽታዬ ጋር ተፋጠናል፡፡ ምስጋና ለአስታማሚዎቼና ለዶክተሮቼ ይግባና አሁን ደህና ነኝ» ሲሉ ህይወታቸው በጤንነትና በህመም አማካይ ቦታ ላይ መቆሙን ይናገራሉ፡፡

ጥበብ ያገለገሏትን ያህል እንዳላገለገለቻቸው አይደብቁም፡፡ «ለጥበብ የሰጡት ይበልጣል ወይስ ጥበብ የሰጠችዎት?» ብላችሁ ብትጠይቋቸው ግልጋሎታቸውንና

ያሉበትን ሁኔታ በማመሳከር «ለጥበብ የሰጠሁት ይበልጣል» ሲሉ ለመናገር አያንገራግሩም፡፡

## ብሔራዊ ስሜት

መርሐዊ ስጦት ከራሳቸው በላይ የሚያስጨንቃቸው የሀገራቸው ጉዳይ ነው፡፡ የወገናቸው መራብና መታረዝ እንባቸውን ያመጣዋል፡፡ ከ1948 ዓ.ም. ጀምሮ ሁሌም በሙሉ ልብስ አምረው፤ በከረባት ደምቀውና ተሽቀርቅረው ቢታዩም ይህ ለእሳቸው ምንም ማለት አይደለም፡፡ ይልቁንም «ብር በጆንያ ሸክፌ ሄዳለሁ» የሚል ከንቱ ህልም ይዘው በማያውቋት አዲስ አበባ ተማምነው መጥተው የሚንከራተቱት የሎተሪ ሻጮች (ሸበላው) ኑሮ እንባ በዐይናቸው እንዲሞላ ያደርጋል፡፡ «የሚበላው፣ የሚለብሰው ባጣ መሀከል ተቀምጦ ፈረንጅ መስሎ መታየት ምን ዋጋ አለው?» ሲሉ ከእንባቸው ጋር እያታገሉና እየተብከነከኑ ገልፀዋል፡፡ «ኢትዮጵያ ደሀ አይደለችም፡፡ ያሏትን እምቅ ሀብቶች አለመጠቀሟ ደሀ አስባላት እንጂ» ብለው ከሚያስቡ ሰዎች ጐራ ይመደባሉ፡፡ «ኢትዮጵያ ለህዝቦቿ በቂ ነች፡፡ እንደውም ለሌሎችም ትተርፋለች፡፡» የሚሉት መርሐዊ ወሎ ውስጥና በተለያዩ በሀገሪቷ ክፍሎች የተጀመሩት ነዳጅን የመፈለግ እንቅስቃሴዎች በተገቢው ሁኔታ ቀጥለው ኢትዮጵያን ሲታደጉ ማየት ትልቁ ምኞታቸው ነው፡፡ «ይህን አይቼ ብሞት ደስ ይለኛል» ሲሉ አጽንዖት ሰጥተው ይናገራሉ፡፡ «ያለ ማዕድን ውጤት 80 ሚሊዮን ህዝብ ማስተዳደር ከባድ ነው፡፡» የሚል እምነት አላቸው፡፡

የኑሮ ውድነት ማየሉ «ስጋ እንበላ ነበር» የሚባልበት ጊዜ ላይ እንዳደረሰን በግርምት ይናገራሉ፡፡ «በደርግ ጊዜ 5 ብር ይሸጥ የነበረን ስጋ የአራት ኪሎ ልኳንዳ ቤቶች 7 ብር ስለሸጡ ታስረው ነበር፡፡ በርበሬ ደብቀው የሸጡ ምላሻቸው ከባድ ነበር፡፡ (በጥይት ይደበደቡ ነበር፡፡) ዛሬ ነጋዴ በህዝብ ላይ አምጿል፡፡ ወገን በወገኑ ላይ ሲያምጽ ያሳፍራል፡፡ በእጅ ስልክ ግንኙነት ገበያው በሰዓታት ሲንር ይታያል፡፡ የነፃ ገበያ ፖሊሲ የታመነበት አልመሰለኝም፡፡» ሲሉ እርምትን የሚሹ ጉዳዮችን በብሔራዊ ስሜት ውስጥ ሆነው ተናግረዋል፡፡

አሜሪካን፣ ሶቭየት ህብረት (ሩሲያ)፣ ቻይናን ጐብኝተዋል፡፡ የዓለምን የኢኮኖሚ ልዕለ ሃያልነት እንደምትቆጣጠረው የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች የሚተነብዩላት ቻይና መመንደግ ትምህርት ሊሆነን እንደሚገባ ይገልፃሉ፡፡ «በ1954 ዓ.ም. ቻይና ውስጥ ቆዳ ጫማ የሚያደርጉት ሹማምንት ነበሩ፡፡ ብዙሐኑ የሚጫማው ሸራ ጫማ ነበር፡፡» የሚሉት ለዛን የታደሉት መርዓዊ ስጦት ዛሬ የቻይናን ታላላቅ ከተሞች ያጣበቡት ዘመነኛ ህንፃዎችና አውቶሞቢሎች፣ የደረሱበትን የዕድገት ደረጃ የሚያሳዩ ውብ ጎዳናዎች በእዚያ ዘመን እንዳልነበሩ በመጥቀስ «እኛ እርስ በርሳችን ስንጨቃጨቅና ስንነዛነዝ እነሱ ጥለውን ሄደዋል፡፡» ሲሉ በመዳህ ላይ ያለውን የኢትዮጵያ የዕድገት ጉዞ ይተቻሉ፡፡ ከምንም በጥረት «ታላቅ» የሆኑት ቻይናዊያን ተሞክሮ ሊኮረጅ የሚገባው

መሆኑን ይጠቁማሉ:: «ሰዎች ቻይናዊያንን በኮሚኒስት መንፈስ ሊያዩዋቸው ይችላሉ:: እኔ እንዲህ አላስብም:: የስራ ሰው መሆናቸውን አይቻለሁ:: በከተማችን የመንገድ ግንባታ ዙሪያ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ታላቅ ነው::» ሲሉ ያወድሳሉ:: «ሀገሩን የሚወድ ለሀገሩ ከእነሱ ይበልጥ ሊሰራ ይገባዋል::»

## አይገረሙም

መኪና ስለሌላቸው፣ 56 ብር እየከፈሉ የቀበሌ ቤት ውስጥ በመኖራቸው፣ አይገረሙም:: በኃይለስላሴ ዘመን ከጓደኛቸው ጋር በጋራ አዲስ ፊያት መኪና በአራት ሺህ ብር ገዝተው ታክሲ አድርገዋት ነበር:: «በወቅቱ የገንዘብን ጥቅም ስለማላውቅ ካቻቩሊና (ጆተኒ) ተጫውቼ ጨረስኩት::» የሚሉት መርዓዊ ገንዘብን መቼ፣ የትና ለምን መመንዘር እንደሚገባ ቢረዱ ኖሮ ጥሩ ቤትና የቤት መኪና ሊኖራቸው እንደሚገባ ያምናሉ:: ይህ የነበረ እውነት እውን ስላልሆነ ግን «ወይኔ» እያሉ ከንፈርን ሲመጡ መኖር አለመዱም:: «ተመስገን» ማለትን ያዘወትራሉ:: ደስተኛ ናቸው:: «መኪና አልመኝም ከኖረኝ ቮልስ ዋገንን የመሳሰሉ ትንንሽ መኪናዎች አልፈልግም:: "ዜንጦ" (ሌክስ) የአርቲስት መኪና እንዲኖረኝ እንጂ» ይላሉ «ኮራ» ብለው::

## የ58 ዓመት ፍቅር

ሙዚቀኛው መርዓዊ ስጦትና የቲያትር ባለሙያው ጌታቸው ደባልቄ ጓደኝነት 58 ዓመት ሞልቶታል:: መርዓዊ «ተንቀሳቃሹ ቤተ-መፃህፍት» ተብለው የሚሞካሹት ጌታቸው ደባልቄን «ጥናት ያደረገ ሰው ካልሆነ በስተቀር የኢትዮጵያን የቲያትር ታሪክ ከጌታቸው የበለጠ የሚያውቅና የሚተነትን ማንም የለም» ሲሉ ያሞካሿቸዋል:: ሁለቱ ባለሙያዎች ያላቸው መግባባትና ፍቅር የሚያስቀና ነው:: በእጅጉ እርስ በእርስ ይደማመጣሉ:: ሁለቱም ከስራቸው በጡረታ የተገለሉ ቢሆንም ሁለተኛ ቤታቸው ብሔራዊ ቲያትርን ሳይሳለሙ መዋል አይሆንላቸውም:: ብሔራዊ ቲያትር መናፈሻ ውስጥ ባለው ፍራንክ አዲስ ካፍቴሪያ ያደነ አያጣቸውም:: መርዓዊ ጋሽ ጌቾን ሲጠሯቸው «ዶክተር» ማለት ይቀላቸዋል::

ጌታቸው በቀድሞ ጊዜ ወደ ካምቦሎጆ ይመጡ እንደነበር ነግረውናል:: «ኳስ በእነ መንግስቱ ወርቁ ጊዜ ቀረ» የሚል አቋም አላቸው:: መርዓዊም በዚህ ይስማማሉ:: ሁለቱም ከልጅነታቸው አንስቶ ፀጉራቸው ነጭ እስኪለብስ ድረስ ያገለገሉት ኪነ-ጥበብ የራሷ ጋዜጣ ስለሌላት ይቆጫሉ:: ጓደኛሞቹ የኖሩለት ኪነ-ጥበብ ዛሬ መድኅን (ዋስትና) ባትሆናቸውም ጥሩውን ጊዜ በትዝታ እያነሱ «ቺርስ» ይባባላሉ::

*ለዚህ ፅሁፍ መሳካት ባልደረባችን **ናፍቆት ዮሴፍ** አስተዋፅኦ አድርጋለች::*